«የዐበይት መናፍቃን '

በሚል ርእስ የተዘጋጀው ጽሑፍ እጅግ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ፣ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተዘጋጀ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ፣ ለብዙ እውነት ፈላጊ ጠያቂዎች በቂ መልስ ይዞ ብቅ ያለ በመሆኑ እጅግ ደስ ብሎኛል:: ለአንባቢያን በፍጥነት ደርሶ ልባቸውን እንዲያሳርፍና የሐሰት መናፍቃንን አፍ ያዝ እንዲያደርግ፣ እንዲሁም በዚህ መጽሐፍ ምንጭነት ትልቁ ወንዝ በስፋት ፈሶ የበርካታ ምዕመናንን ጥማት እንዲያረካ ምኞቴና ጸሎቴ ነው»::

መጋቢ ዮሐንስ ባሣና
(ኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን)

«አሳች እስካለ ድረስ ያልተጠነቀቀ ያላወቀና ያላስተዋለ ሁሉ ሊስት ይችላል:: ዓለማችን በአሳቾች እየተጥለቀለቀች ነው:: በአሁኑ ጊዜ ተጠንቀቁ፣ አስተውሉ የሚሉ ሰዎችን እንደ አሉታዊ መልእክተኛ በማየት የሚያወግዙ ሰዎች፣ «መንፈስ ቅዱስ ይመራኛል፤ ማንስ ያታልለኛል» በሚል ዐጉል ፈሊጥ፣ የቃሉን የእውነት ምሪት የኋሊት አሽቀንጥረው ወደ ዘላለም ጥፋት እየተክነፈነፉ በመጥፋት ላይ ናቸው::

ሁላችንም ሰይጣን በተባለው አሞኝትና በተከታዮቹ እንዳን ታለል፣ ይህ ጽሑፍ በእግጅጉ ይጠቅማል:: በተለይ ለመጋቢያን፣ ለወንጌላውያን፣ ለመምህራን እንዲሁም ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተማሪዎች እጅግ ታላቅ ጠቀሜታ አለው:: ይነበብ፤ ይደገም፤ ይሠለስ»::

ዶ/ር ጣላርጌ የሺድንበር
(አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት)

«ከተስፋዬ በፊት በመናፍቃና አስተምህሮ ላይ መልስ የሰጠ አንድም ሰው የለም (ቢያንስ እኔ እስከማውቀው)። በዚህ ረገድ ተስፋዬ ሮበሌ ባለ ውለታችን ነው ብል ዕብለት አይሆንብኝም። ስሕተትን በደፈናው ኰንኖ መቀመጥ ምንም አይፈይድም። ይህ መጽሐፍ ግን እንዲህ አይደለም። ስሕተቱን ነቅሶ ትክክለኛውንና እውነተኛውን መልስ፣ ቃለ እግዚአብሔርን ዋቤ አድርጎ ይሰጣል እንጂ። ጥቅስን ከዐውደ ንባብ አፋተው ለሚተረጕሙ መናፍቃን መስጠት የሚገባንን መልስ ይጠቁመናል። ይህ ታዲያ «ሰሙ» ነው። ለእውነት መቆም ከክርስቲያኖች ሁሉ የሚጠበቅ ኀላፊነትም እንደ ሆነ ያሳስበናል። ይህ ደግሞ «ወርቁ» ነው»።

ምኒልክ አሰፋው
(ኢንተርናሽናል ባይብል ሦሳይቲ )

«በሐዋርያው ጳውሎስና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዘመን በትንግርት ይታይ የነበረው የሐሰት ትምህርት፣ እኛ ባለንበት በዚህ ዘመን እንደ አሸን ፈልቶአል። በቅንነት እግዚአብሔርን የሚፈልጉትንም ሰዎች ልብ በድንገት ሰርቆ አንገላቶአቸዋል። የኋላ ኋላ ግን የተሳሳቱ እንኳ በጥልቀት ስመረምሩ የሐሰተኞች ትምህርት መሠረተ ቢስ መሆኑን ተረድተው ወደ እውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል ተመልሰዋል።

«ዛሬም በኢትዮጵያ የምታየው የሐሰት ትምህርት ግርግር እንደ አገዳ እሳት ውስጠ ባዶነቱ እያደር ይገለጣል። አቶ ተስፋዬ ሮበሌ እውነትን በፍቅር ለመግለጥ በሚቃጠል ልብ በሐሰት ትምህርት ላይ ሰፊ ጥናት ባካሄደው ውስጥ በጥቅቱ በዚህ ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ ያቀረባቸው ግልጽ ማስረጃዎች ብዙ ወገኖች ለጥያቄያቸው መልስ የሚያገኙበት ከመሆኑም በላይ ተሳስተው እሩቅ መንገድ ለሄዱትም የእውነት ማንቂያ ደወል ይሆናቸዋል።»

ኩርሴ ሸፈኖ
(ኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን)

«በመናፍቃን ማንነትና በትምህርታቸው ላት ያተኰረ እንዲህ ዐይነት መጽሐፍ በወንድም ተስፋዬ ሮበሌ መጻፉ እጅግ የሚያስደስት ነው። ብዙ ጌታን ዐውቀናል የሚሉ ምዕመናን፣ በመጣው የትምህርት ነፋስ ሁሉ ወዲህና ወዲያ በሚሉበት በአሁኑ ወቅት፣ እንዲህ ያለው መጽሐፍ ቤተ ክርስቲያን የመናፍቃንን ትምህርት እንድትረዳና ምዕመኖቿንም ከትምህርታቸው እንድትጠብቅ የሚሰጠው ጠቀሜታ የላቀ ስለሆነ፣ ሁሉም አማኝ በተለይም አገልጋዩች ሊያነቡት የሚገባ መጽሐፍ ነው»።

ስምዖን ሙላቱ
(ፕሪንሲፓ ል)
ኢቲሲ.

«ሰፊ ከሆነው ከእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በሚወሰድ ቊንጽል ሐሳብ ወይንም ተገለጠልን በሚባል በሌላ ሃሳብ ዙሪያ የእግዚአብሔርን እውነት ሁሉ ለማስለፍ መጣር፣ ከብዙ የስተት ትምህርቶች መሠረታዊ ባሕርያት አንዱ ነው። እንደዚህ ዐይነት ትምህርቶች በሰዎች አእምሮ ለሚመላለሱ ጥያቄዎች አቋራጭ መልስ የሚሰጡ፣ ለኑሮ ችግሮች አፋጣኝ መፍትሔ የማምጣት መሰል ባሕርይ አላቸው፤ በተለይ በአሁኑ ዘመን ብዙዎች ወደ ስሕተት ትምርቶች በመግባት ላይ እንዳሉ እናስተውላለን። ይህች መጽሐፍ በስሕተት ጐዳና ያሉትን ወደ ትክክለኛው ትምህርት ለመመለስ፣ ሌሎችን ደግሞ ከስሕተት ለመጠበቅ የሚረዳ ግንዛቤን የሚያስጨብጥ መልክት ያዘለች ናት። በመሆኗም አብያተ ክርስቲያናትና መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች በትምህርት መሣሪያነት ቢጠቀሙባት መልካም ነው እላለሁ»

አታላይ ዓለም (ዶ/ር)

## የመጽሐፉ መታሰቢያነት

በቃልና በምግባር አርአያ ለሆነኝ ለምወደውና ለማከብረው ለአቶ ሰሎሞን ከበደ እንዲሁም ለአዲሱ መደበኛ ትርጒም ሥራ ተሳታፊዎች በሙሉ::

# ዐበይት መናፍቃን

ከተስፋዬ ሮበሌ

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
የሥነ ጽሑፍ አገልግሎት
የመልእክት ሣጥን ቍጥር 5829
አዲስ አበባ

- ርእስ - ዐበይት መናፍቃን
- Title - Major Cults


- ጸሓፊ - ተስፋዬ ሮበሌ
- Author - Tesfaye Robele


- አሳታሚ - የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የሥነ ጽሑፍ አገልግሎት
- Publisher:- Ethiopian Kale Heywet Church Literature Department


- መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
- Copyright 2001 - Kale Heywet Literature Department
- ያለ አሳታሚው ፈቃድ አባዝቶ ማሳተምም ሆነ የተወሰነን ክፍል በተለያዩ መንገዶች ማራባት በጥብቅ የተከለከለ ነው:: በማንኛውም መልኩ መረጃዎችን ለመውሰድ ከተፈለገ፣ በትክክል ሥርዐቱን ጠብቆ ሊጠቀስ፣ በግርጌ ማስታወሻ ሊመላከት ይገባዋል::
- All rights reserved. No part of this publication may be reproduced, stored in a retrieval system, or transmitted in any form or by any means-electronic, mechanical, photocopying, recording, or other wise-without the prior written permission of the publisher and copyright owner.


- ልዩ መግለጫ ካልተሰጠ በስተቀር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀምነው የጐርጐሮሳውያን የዘመን አቈጣጠር ነው::
- ልዩ ማብራሪያ ካልቀረበ በስተቀር የተጠቀምነው የኢትዮጵያ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር 1954ዓ.ም ያሳተመውን የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው::
- ጥያቄ አስተያየትም ሆነ ሒስ ካልዎት ለጸሓፊው በሚከተለው አዲራሻ ይጻፉ:-


ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር

የመ.ሣ.ቍጥር 23045፣ ኮድ 1000

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ


- Comments, questions, and Criticisms of this book are welcome. Please address all correspondence to:-


Tesfaye Robele,

Tesfa Evangelical Society For Apologetics,

P.O. Box 23045 , Code 1000

Addis Ababa, Ethiopia.


# ማውጫ


፩. **ክፍል አንድ:-** ስለ መናፍቃን ማጥናት ለምን አስፈለገ? 1

ይህን መጽሐፍ መጻፍ ለምን አስፈለገ? 1

፪ **ክፍል ሁለት:-** ኑፋቄ የሚለው ቃል ምን ትርጕም ይወክላል? 7

ኑፋቄ ማለት ምን ማለት ነው? 7

ሀ. የቃሉ ቋንቋዊ አጠቃቀም 7

ለ. ነገረ መለኮታዊ አጠቃቀም 9

ሐ. የነገረ መለኮት አጠቃቀሙ ትንታኔ 11

፫ **ክፍል ሦስት:-** በመናፍቃን ተዘውትረው የሚታዩት ባሕርያት የትኞቹ ናቸው? 17

ሀ. የመናፍቃን አስተምህሮአዊ ባሕርይ 17

ለ. ተመሳሳይ የሆኑ የመናፍቃን አስተምህሮአዊ ባሕርያት 18

፬ **ክፍል አራት:-** የመናፍቃን ዕድገት ምን ይመስላል? 43

ሀ. የመናፍቃን ስታቲስቲክስ 43

ለ. የይሖዋ ምስክሮች ዓለም ዐቀፋዊ ስታቲስቲክስ 43

ሐ. የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክስ በኢትዮጵያ 47

መ. የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ስታቲስቲክስ በኢትዮጵያ 49

ሠ. የሞርሞኖች ዓለም ዐቀፋዊ ስታቲስቲክስ 53

ረ. የበሃኢ እምነት ስታቲስቲክስ በኢትዮጵያ 57

፩ ክፍል አምስት፡-መናፍቃን የመበራከታቸው ምስጢር ምንድን ነው? 59

ሀ. ሰዎች መናፍቃንን ለምን ይከተላሉ? 59

ለ. ሰዎች መናፍቃንን በመጠጋት ሊያሟሏቸው የሚሹአቸው ፍላጎቶች 63

፩ ክፍል ስድስት፡- የመናፍቃንን ዕድገት ለመቀነስ ልንወስዳቸው የሚገቡ ርምጃዎች የትኞቹ ናቸው? 67

ሀ. ሰዎች መናፍቃንን እንዳይከተሉ እንዴት ልንጠብቃቸው እንችላለን? 67

ለ. መናፍቃን ሐሰተኞች መሆናቸውን ለቤተ ክርስቲያንህ ማሳየት 68

ሐ. መናፍቃን ሐሰተኞች መሆናቸውን ለልጆች ማሳየት 73

፩ ክፍል ሰባት፡- የይሖዋ ምስክሮች ከየት እስከ የት? 77

ሀ. የይሖዋ ምስክሮች ታሪካዊ ዳራ 77

ለ. የይሖዋ ምስክሮች ታሪክ በኢትዮጵያ 83

፩ ክፍል ስምንት፡- ትምህርተ ሥላሴ የተቀዳው ከቃለ እግዚአብሔር ወይስ ከአረማውያን መድበለ አማልክት? 87

ሀ. የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮተ ሥላሴ 87

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥላሴ ምን ያስተምራል? 101

፩ ክፍል ዘጠኝ፡- ትንሣኤ የአካል ወይስ የመንፈስ? 103

ሀ. የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ 10

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ምን ይላል?109

፩ ክፍል ዐሥር፡- ደኅንነት በሥራ ወይስ በጸጋ? 119

ሀ. ደኅንነት እንደ ይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ 119

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ደኅንነት ምን ያስተምራል? 133

፩ ክፍል ዐሥራ አንድ፡- አብና ወልድ---አንድ ወይስ ሁለት አካል? 139

«ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንና» ትምህርተ ሥላሴ 139

፩ ክፍል ዐሥራ ሁለት፡- የክርስትና እምነት ከባሃኢ ሃይማኖት ጋር ማበር ይችላልን? 163

ሀ. የባሃኢ እምነት ታሪካዊ ዳራ 163

ለ. የባሃኢ እምነት በኢትዮጵያ 164

ሐ. የባሃኢ እምነት አስተምህሮ 167

መ. የባሃኢ ሃይማኖትና ክርስትና 168

፩ ክፍል ዐሥራ ሦስት፡- የሞርሞን ሃይማኖት ክርስትና ነውን? 173

ሀ. የሞርሞን እምነት ታሪካዊ ዳራ 173

ለ. የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን ዐዋጆች 176

ሐ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሞርሞን እምነት ምን ይላል? 178

መ. የሞርሞን አስተምህሮ 179

ሠ. የሞርሞን መጽሐፍና የሥነ ቅርስ ጥናት 181

# መቅድም

የመናፍቃን መበራከት እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሶአል። እውነት ደግሞ እውነት መሆኑ የሚታወቀው፣ ሐሰት ሐሰት መሆኑ ይፋ ሲወጣ ነው። ብዙ ክርስቲያኖች መናፍቃንን በወንጌል የማይደርሷቸው፣ ወንጌል ለመናፍቃን እንደሚያስፈልግ አጥተውት ወይም የመናፍቃን ጉዳይ ግድ ስለማይላቸው አይደለም፤ ነገር ግን ስለ መናፍቃንና ስለ አስተምህሮአቸው በቂ ዕውቀት ስለ ሌላቸው እንዲሁም የወንጌልን እውነት እንዴት ማስተላለፍ (ማቀበል) እንዳለባቸው ስለማያውቁ ነው።

ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ የተነሣሣሁት፣ ይህንን ዐሳብ ትንሽ ታህል እንኳ ፊቅ ባደርገው ብዬ ነው። ይህ መጽሐፍ የተጻፈው ክርስቲያኖች በአገራችን ውስጥ ዐበይት የሆኑትን የመናፍቃን አስተምህሮ መሠረታዊ ትምህርት እንዲያውቁ ታስቦ ነው። ስለዚህ የመጽሐፉ የመጨረሻ ገጽ ላይ ስትደርሱ፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት መናፍቃን የሚያነሡአቸውን ወይም ያላቸውን አስተምህሮአቸው ጥያቄዎች ሁሉ መልስ መስጠት ትችላላችሁ ባልልም፣ ቢያንስ መሠረታዊ አስተምህሮዎችን በተመለከተ ክርስቲያን ምን እንደሚያምንና ለምንስ በዚያ መልኩ ማመን እንዳስፈለገው (እንዳለበት) ማሳወቅ ቢያስችል ብዬ ነው።

## መሠረታዊ ነጥቦች

1. በሚወያዩበት ጊዜ አይቈጡ። ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ አቴና ሲገባ ከተማዋ በጣዖት በመሞላቷ እንደ ተቈጣ እናነባለን (ሐሥ 17 ÷ 16)። ነገር ግን ከአቴና ሰዎች ጋር ይወያይ የነበረው፣ ትሕትናና ከበሬታ በተሞላበት ሁኔታ ነበር። ውይይቱንም የሚጀምረው እርሱም ሆነ የአቴና ጣዖት አምላኪዎች ከተቀበሉት

የጋራ እውነት በመነሣት ነበር «...የአቴና ሰዎች ሆይ፤ እናንተ በሁሉ ነገር አማልክትን እጅግ እንደምትፈሩ እመለከታለሁ:: የምታመልኩትን እየተመለከትሁ ሳልፍ፣ ለማይታወቅ አምላክ የሚል ጽሕፈት ያለበትን መሠዊያ ደግሞ አግኝቼአለሁና:: እንግዲህ ይህን ሳታውቁ የምታመልኩትን እኔ እነግራችኋለሁ» (ሐሥ 17÷22-23)::

2. ውይይት ተገቢ ነገር እንደሆነ በግልጽ ያስረዱ:: አንድ ሃይማኖት መሠረተ እምነቱ ትክክል መሆኑን መመርመር አንገብጋቢ ጉዳይ እንደሆነ ከመግለጽ አይቦዝኑ::

3. በአንድ ጊዜ በአንድ ርእሰ ጉዳይ ላይ ብቻ ይወያዩ:: መሠረታዊ ከሆኑትና በደንብ ካጡኑአቸው ትምህርቶች ውስጥ አንዱን ርእሰ ጉዳይ ብቻ ለውይይት ይምረጡ:: ወደሌላ ርእስ የሚያልፉት ይህን ርእሰ ጉዳይ ከቋጩ በኋላ ይሁን:: ብዙ መናፍቃን ከጥቅስ ወደ ጥቅስ መዝለል ስለሚወዱ፣ አንዱን ጥቅስ በበቂ ሁኔታ ከተወያዩበት በኋላ ወደሌላው እንዲያልፉ ያበረታቷቸው::

4. እውነትን ከማስተማር ውጪ እውነትን እንዲቀበሉ አያስገድዱ:: ሰዎች መሳሳታቸውን እያወቁ ተሳስቻለሁ ላይሉ ይችላሉ:: ስለዚህ ወደ ቤታቸው ሄደው እንዲያስቡበት ይፍቀዱላቸው::

5. የማያውቁትን ነገር አይናገሩ:: በዕብራይስጥና በግሪክ ቋንቋዎች ላይ ያልዎት ዕውቀት ጠንካራ ካልሆነ፣ ጠለቅ ባለ ሰዋስዋዊ ጉዳዮች ላይ አይነጋገሩ:: እርግጠኛ ባልሆኑባቸው ርእሰ ጉዳዮችም ላይ አይወያዩ:: የሚጠየቁትን ጥያቄ የማያውቁት ከሆነ ያለማወቅዎትን በግልጽና በትሕትና ያስረዱ:: ለጥያቄውም መልስ እንደሚፈልጉለት ይግለጹ::

6. በውይይቱ እግዚአብሔር እንዲረዳዎት ይጸልዩ:: ጸሎት እግዚአብሔርን እርዳታ የመጠየቅያ መንገድ ነውና::

# ክፍል አንድ

## ስለመናፍቃን ማጥናት ለምን አስፈለገ?

## ይህን መጽሐፍ መጻፍ ለምን አስፈለገ?

ይህን መጽሐፍ መጻፍ ያስፈለገው፣ ስለ መናፍቃንና ስለ አስተምህሮአቸው ማጥናት አስፈላጊ በመሆኑ ነው:: ስለመናፍቃንና ስለ አስተምህሮአቸው ማጥናት ያስፈለገበት ምክንያት:-

### 1.መጽሐፍ ቅዱስ ለመናፍቃንና ለትምህርታቸው ትልቅ ትኩረት ስለሚሰጥ

የነገረ መለኮት ሊቃውንት፣ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከሚያስተምሩአቸው ትምህርቶች ውስጥ ስለ መናፍቃን የተሰጠው ትምህርት፣ ከአጠቃላዩ ትምህርት ሦስት አራተኛውን እንደሚይዝ ያስረዳሉ:: ይህ እውነት ቅዱሳት መጻሕፍት ለመናፍቃንና ለትምህርታቸው ምን ያህል ትኩረት እንደሰጡና እኛም ለጉዳዩ ትልቅ ትኩረት በመስጠት ስለ መናፍቃን ማጥናት እንዳለብን ያስገነዝበናል (ዮሐ 10÷12፤ ማቴ 7÷15፤ 24÷11፤ ማር 13÷22፤ ማቴ 5÷19፤ 15÷9፤ 1ጢሞ1÷7፤ 4÷2፤ 1ጴጥ3÷15፤ ማቴ 12÷34:39፤ ማቴ 13÷15፤ 21÷23-25፡ 27÷28፡ 33፤ ማቴ15÷14)

### 2. ክርስቲያኖች እምነታቸውን ከመናፍቃን መጠበቅ ስላለባቸው

ሐዋርያት፣ «ወዳጆች ሆይ፣ ስለምንካፈለው ስለ መዳናችን ልጽፍላችሁ እጅግ ተግቼ ሳለሁ፣ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለተሰጠ

ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ» (ይሁዳ 3)። «በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፤ ነገር ግን በየዋህነትና በፍረሀት ይሁን» (1ጴጥ3÷15) ይሉናል። በትምህርታቸውና በስብከታቸውም የመናፍቃንን ትምህርት ይኰንኑ ነበር (ሐሥ 2÷14-41፤ 3÷12-26፤ 4÷8-12፤ ሐሥ 6÷8-10፤ 7÷1-60፤ 13÷8-12 16-46፤ 14÷1-4፤ 17÷1-4፤ 16-34)።

የእምነት አባቶች የምሥራቹን ቃል ከሚሸቃቅጡ መናፍቃን ጠብቀው ለእኛ እንዳስተላለፉልን፤ እኛም ጤናማውን ወንጌል ጠብቀን የማቆየት ዐደራ አለብን። ይህ ደግሞ የሚሆነው የመናፍቃንን አስተምህሮ በሚገባ ስናውቅ ነው።

*3. በከፍተኛ ፍጥነት በመስፋፋት ላይ ያለውን መናፍቃዊ ትምህርት ጤናማ በሆነ አስተምህሮ መመከት (መገደብ) ስለሚያስፈልግ*

ብዙ መናፍቃዊ እንቅስቃሴዎች የተጀመሩት፤ በዐሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደሆነ መረጃዎች ይገልጻሉ። እንዲያውም ይህ እኛ ያለንበት ዘመን፤ «መንፈስ ግን በግልጥ፦ በኋለኞቹ ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፤ ሃይማኖትን ይክዳሉ» (1ጢሞ4÷1) የሚለው ትንቢት የተፈጸመበት ጊዜ ይመስላል።

መናፍቃን ከሰናፍጭ ቅንጣት በእጅጉ ከሚያንሰው አቶም [atom] ያነሰ ጅማሬ ቢኖራቸውም፤ የአቶም በምብ ከሚያስከትለው ውድመት የበለጠ ጥፋት እያመጡ ነው። ስለዚህ አማኞች፤ «...ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም መጥተዋልና» (1ዮሐ 4÷1) የሚለውን ቃል በማጤን ማንነታቸውን ሊያውቁ፤ እንደ እግዚአብሔርም ቃል ሊቃወሟቸው ይገባል።



ከኒቂያ ጉባኤ በፊት የነበሩ አበው [ለምሳሌ፦ ዮስጦስ ሰማዕት፣ ሔሬኔዎስ፣ ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ፣ ጠርጡልያኖስ] እምነታቸውን ከአይሁዶች፣ ከጣዖት አምላኪዎች፣ ከኖስቲኮች እንዲሁም በዘመናቸው ከተነሡት መናፍቃዊ ትምህርቶች ሁሉ ጠብቀዋል።

በመካከለኛው ዘመን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ታስተምረው የነበረውን ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት በመቃወም፣ ጤናማውን አስተምህሮ ያቀበሉንን የተሐድሶ መሪዎች በዚህ ቦታ ልንዘክራቸው ይገባል። ስለዚህ በከፍተኛ ፍጥነት በመሠራጨት ላይ ያለውን መናፍቃዊ ትምህርት፣ ጤናማ በሆነው አስተምህሮ መመከት የምንችለው የመናፍቃንን ማንነትና አስተምህሮ ጠንቅቀን ስናውቅ ብቻ ነው።

*4. መናፍቃን ወደ ክርስቶስ መምጣት ስላለባቸው*

መናፍቃን እንደ ማንኛውም ሰው መዳን ያስፈልጋቸዋል። ወደ ጠፉ ሰዎች መሄድ ደግሞ የክርስቲያኖች ሁሉ ኀላፊነት ነው። እግዚአብሔር ዐደራ ሰጥቶናል። ያም ዐደራ ለሰዎች ሁሉ እውነተኛውን የምሥራች ቃል መንገር ነው።

አንድ ሐኪም የሕመምተኛውን በሽታ ከተረዳ በኋላ፣ ለበሽታው የፈውስ መድኀኒት እንደሚሰጠው ሁሉ፣ እኛም በዘመናችን ያሉትን መናፍቃን ወደ ክርስቶስ ማምጣት የምንችለው የአስተምህሮአቸውን ጠማማነት በሚገባ ስናውቅ ብቻ ነው።

*5. ቤተ ክርስቲያን አባሉቿን ከመናፍቃን መጠበቅ ስላለባት*

ቤተ ክርስቲያን አባሉቿን ከመናፍቃን የመጠበቅ ኀላፊነት አለባት። ኀላፊነትና ተጠያቂነት ደግሞ እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሄዱ

ነገሮች ስለሆኑ፣ ዛሬ የተሰጠን ኀላፊነት ነገ እንደሚያስጠይቀን መገንዘብ ይገባናል።

ቤተ ክርስቲያን አባሎቿን ከመናፍቃን መጠበቅ የምትችለው የመናፍቃንን ከንቱ ትምህርት ለአባሎቿዋ ገላልጣ ስታሳይ ብቻ ነው።

*6. መጥፎ አስተምህሮ አገርንና ሕዝብን ስለሚጐዳ (ስለሚያነቅዝ)*

ትምህርት፣ ምግባርን አስከትሎ ይሄዳል። መጥፎ ትምህርትን የተቀበለ ሰው መጥፎ ፍሬ ያፈራል። የእግዚአብሔር ቃል፣ «ከእሾኽ ወይን፣ ከኵርንችትስ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፤ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል፤ መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም» (ማቴ 7÷16-18) የሚለው ለዚህ ነው።

መጥፎ አስተምህሮ አገርንና ሕዝብን ይጐዳል። «አንድ ክርስቲያን ሥራን በመሥራት ሳይሆን የሚፈልገውን ነገር እንደ ሆነለት (እንደሚሆንለት) በማመኑ ብቻ የሚሻውን ነገር ያገኛል» የሚለውን የእምነት እንቅስቃሴ መምህራንን ትምህርት የተቀበሉ ከ20 በላይ የአዲስ አበባ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች፣ በዩኒቨርስቲው የሚያቀያቸውን ውጤት ማምጣት ባለመቻላቸው ከትምህርት ቤቱ መባረራቸውን አንድ መንፈሳዊ ድርጅት አስታውቋል። ይህ ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለአገር ትልቅ ጕዳት ነው።



*7. መናፍቃንን በተመለከተ የምናጠናው ትምህርት እምነታችንን ስለሚያጸና።*

መናፍቃንን መናፍቃን የሚያሰኛቸው፣ መሠረታዊ የሆኑትን የቃለ እግዚአብሔር ትምህርቶች ባለመቀበላቸው ነው። አንድ ክርስቲያን ራሱንም ሆነ ቤተ ክርስቲያኑን ከመናፍቃን እንቅስቃሴ ለመጠበቅ እንዲሁም መናፍቃንን በወንጌል ለመድረስ በሚያደርገው ጥናት፣ መሠረተ እምነቱ ምን እንደሆነና ለምን በዚያ መልኩ ማመን እንዳስፈለገው እንዲያውቅ ይረዳዋል።

*8. ቤተ ክርስቲያን ከመናፍቃን መማር ስለሚገባት*

መናፍቃን ሐሰተኞች ስለሆኑ፣ «ከእነርሱ የምንማረው አንዳች ነገር የለም» ብሎ ማሰብ ቂልነት ነው። መናፍቃን ሰዎችን የሚስቡበት ትምህርት እውነት ባይሆንም እንኳ ሰዎች የሚፈልጉት ነገር እነርሱ ዘንድ አለ ማለት ነው።

መናፍቃን ከፍተኛ ትኵረት የሚሰጡት በቤተ ክርስቲያን ደካማ ጐኖች ላይ ስለሆነ፣ ለእነርሱ ዕድገት ምክንያት የሆኑትን ነገሮች በመመርመር፣ ቤተ ክርስቲያን ድካሟን አሻሽላ መቅረብ ይኖርባታል። ይህ ደግሞ ሊሆን የሚችለው ስለ መናፍቃንና ስለ አስተምህሮአቸው ስናውቅ ብቻ ነው።

# ክፍል ሁለት

# ኑፋቄ የምለው ቃል ምን ትርጉም ይወክላል?

## ኑፋቄ ማለት ምን ማለት ነው?

ከቋንቋ አጠቃቀም የምንማረው ነገር፣ አብዛኛውን ጊዜ አንድ ቃል ከአንድ በላይ ትርጉም ሊወክል እንደሚችል ነው። የቃሉን አማራጭ ትርጉም የሚወስነውም፣ ቃሉ የሚገኝበት ዐረፍተ ነገር ወይም ዐውድ ነው። ከዚህ በመቀጠል «ኑፋቄ» የሚለውን ቃል ቋንቋዊ ፍቸውንና ነገር መለኮታዊ አጠቃቀሙን በስፋት ለመመልከት እንሞክራለን።

### ሀ. የቃሉ ቋንቋዊ አጠቃቀም

«ኑፋቄ» የሚለው ቃል ከግእዝ ቋንቋ የተወረሰ ሲሆን፣ የኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤ _መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ_ (ገጽ 645-646) ቃሉን በዚህ መልኩ ይፈታዋል:-

- ነፈቀ፤ (ነፈቀ:ይነፍቅ:ይንፈቅ)፤ መንፈቅ መሠንጠቅ፤ አስተካክሎ መክፈል መለየት።
- መናፍቅ፤ ( ቅት ቃን ቃት)፤ ናፋቂ፣ አናፋቂ፤ የሚጠራጠር ፤ ጠርጣሪ አጠራጣሪ፤ ሃይማኖቱ ሕጹጽ የኾነ፤ ምሉእና ፍጹም ትክክል ያይደለ፤ መንፈቁን አምኖ መንፈቁን የሚክድ።

- ኑፋቄ፤(ያት)፤ በቁሙ፤ መክፈል፣ መከፈል፤ ክፍያ አከፋፈል ጥርጥር፣ ጥርጠራ፤ ምንታዌ።

እንደ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ ኑፋቄ የሚለው ቃል «ነፈቀ» ከሚለው ቃል የወጣ ሲሆን፣ ትርጉሙም አንድን ነገር አስተካክሎ ለሁለት መክፈል፣ ማመንታት ወይም መጠራጠር፣ እምነተ ሰንካላ መሆን፣ ግማሹን አምኖ ግማሹን መካድ በአጠቃላይ ሃይማኖቱ ሕጹጽ (ጐደሎ) የሆነ ማለት ነው።

ኑፋቄ የሚለው ቃል ከግእዝ የመጣ ቢሆንም፣ የአማርኛ ፍቺውን መመርመር፣ የቃሉ አማራጭ ትርጉም እስከምን ድረስ እንደሆነ ለማወቅ፣ የአማርኛ መዝገበ ቃላትንም መመልከት መልካም ነው። ከሣቴ ብርሃን ተሰማ፤ _የዐማርኛ መዝገበ ቃላት_፤ ቃሉን በሚከተለው መልክ ይፈታዋል።

- ነፈቀ፤ ዐመትን ዕለትን ወርን ከፈለ፣ ለየ ወይም አንድ ሙሉ የኾነ ነገርን ከኹለት ከፈለ ወይም የብርቱካንን፣ የሎሚን አካል ክፍልፋሎች በየክፍላቸው ለየ።
- ነፈቀ፤ ከሃይማኖት ወጣ፤ ተጠራጠረ፤ መናፈቅን፣ ከሓዲን ኾነ ነፈቀ።

የአማርኛው ገለጻ በአብዛኛው ከግእዙ ጋር አንድ ዐይነት ቢሆንም፣ «ከሃይማኖት መውጣት፣ ከሓዲ መሆን» የሚለውን ትርጉም ጨምሮአል። በአጠቃላይ ኑፋቄ የሚለው ቃል ቋንቋዊ አጠቃቀሙ፡- _«አንድን ነገር ለሁለት አስተካክሎ መክፈል፤ ማመንታት ወይም መጠራጠር፤ ግማሹን አምኖ ግማሹን በመካድ፤ እምነተ ሰንካላ ወይም ከሓዲ መሆን» ማለት ነው።_



## ለ. ነገረ መለኮታዊ አጠቃቀም

ኑፋቄ ወይም መናፍቅ ለሚለው ቃል የእንግሊዝኛ አቻ ቃላት ክልት ( CULT) እና ሔረሲ (HERESY) የሚሉት ናቸው።

ክልት የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ክልተስ ከሚለው የላቲን ቃል የተወረሰ ሲሆን ትርጉሙም፡- «ማምለክ ወይም ለመለኮት ክብርን መስጠት»[1] ማለት ነው። የላቲን ቨልጌት ቃሉን ለእውነተኛው አምላክም ሆነ ለጣዖታት የሚቀርበውን አምልኮ በሚያሳይ መልኩ ተጠቅሞበታል። ለምሳሌ በሐዋርያት ሥራ 17÷23 ላይ የአቴና ሰዎች ለሚያመልኳቸው ጣዖታት ይቀርብ የነበረውን አምልኮ ሲያመላክት፣ በቍጥር 25 ላይ ደግሞ፣ « ሕይወትንና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ» ለሚሰጠው ልዑል እግዚአብሔር የሚሰጠውን አምልኮና ክብር ለማሳየት ቃሉ ጥቅም ላይ ውሎ እንመለከታለን[2]። ይህ ትርጉም እኛ ልንጠቀምበት ካሰብነውና ዛሬ እየተሠራበት ካለው አጠቃቀም ብዙ የራቀ ስለሆነ፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አንጠቀምበትም።

ሔረሲ የሚለው ቃል፣ «ሔረሲስ» ከሚለው የግሪክ ቃል የተወረሰ ሲሆን፣ ትርጉሙም፣ « ምርጫ » ወይም « የተመረጠ » ማለት ነው። ቃሉ በአዲስ ኪዳን ግሪክ ጥቅም ላይ የዋለው «ክፍፍል» በሚለው ትርጉሙ ነው ( የሐሥ 24÷14፤ 1ቆሮ 1÷119፤ ገላ 5÷19-20 ይመለከቷል)። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሔረሲ የሚለውን ቃል ትገለገልበት የነበረው፣ መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎችን ለሚቃወም ግለሰብ ወይም እንቅስቃሴ ሲሆን፣ ክርስቲያኖች ከእንዲህ ዐይነቱ ሰው ወይም እንቅስቃሴ መራቅ ወይም መለየት

[1] Charlton T. Lewis and Charles Short, A Latin Dictionary ( Oxford:Oxford University Press, 1879, Impression of 1984) S.V. " Colo " 370. ላይ Alan W. Gomes, Unmasking the Cults ( Grand Rapids: Zondervan, 1995) በገጽ 7 ላይ ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[2] Gomes ገጽ 7።

እንዳለባቸው በሚገልጽ መልኩ ገብቶአል[3] (የሐሥ 24÷14 ይመለከቷል):: ስለዚህ ሔረሲ ማለት መሠረታዊ የሆነውን ክርስቲያናዊ ትምህርት መካድ ስለሆነ፣ ከልት ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ትርጒም አለው::

በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጁ አንዳንድ የነገረ መለኮት መጻሕፍት ከልትና ሔረሲ ከሚባሉት ቃላት በተጨማሪ፣ አከልት (Occult) እንዲሁም ሴክት (Sect) የሚሉትን ቃላት ሲጠቀሙ ይስተዋላል:: ከዚህ የተነሣም ስለ እነዚህ ቃላት ትንሽ መወያየቱ አግባብነት ይኖረዋል::

ያከልት የሚለው ቃል ያከልተስ (Occultus) ከሚለው የላቲን ቃል የመጣ ሲሆን፣ ትርጒሙም፣ «የተደበቀ» ወይም «ምስጢር» ማለት ነው:: የአማርኛ ጸሐፎች ለዚህ ቃል የሚሰጡት ትርጒም የተለያየ ሲሆን [አስማተኛ፣ ድግምተኛ፣ መተተኛ፣ ጠንቋይ፣ ቃላተኛ፣ መናፍስት ጠሪ፣ ዕድል ነጋሪ] አብዛኞቹ የሚስማሙበት ቃል ግን «ጥንቈላ» የሚለውን ነው:: አንዳንድ መጻሕፍት እንደሚያስተምሩት ጥንቈላ (አከልት) በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች የሚከፈል ሲሆን፣ እነዚህም (1) መናፍስት ጠሪነት (2) ዕድል ነጋሪነት እንዲሁም (3) አስማት ናቸው[4]:: እነዚህም ነገሮች የሚከናወኑት ሞራ በመግለጥ፣ ጠጠር በመጣል ወዘተ ባሉት መንገዶች ነው::

አሜሪካን ሄሪቴጅ የሚባለው የእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት «ሴክት» የሚለውን ቃል፣ «ሰፊና ትልቅ ከሆነው ሃይማኖት ተገንጥሎ የወጣ ሃይማኖታዊ አካል» ሲል ይፈታዋል[5]:: ብዙ የትምህርተ መለኮት መዝገበ ቃላት፣ «ሴክት» የሚለውን ቃል የሚጠቀሙበት ክርስቲያኖች

---

[3] Boman, Orthodoxy and Heresy ገጽ 50::

[4] George A. Mather and Larry A. Nichols, Dictionary of Cults, Sects, Religions and Occult ( Grand Rapids: Zondervan, 1993) ገጽ 212::

[5] American Heritage Dictionay, Second Collge Editi.n ( Boston:Houghton Mifflin, 1985,) ገጽ 1108::



ሆነው የሃይማኖት ባለሥልጣናትን የማይቀበሉ እንዲሁም ከቤተ ክርስቲያን ራሳቸውን ያገለሉ፣ ነገር ግን ጥለውት የሄዱት ቤተ ክርስቲያን አጒድሎታል የሚሉትን ትምህርት አጠንክረው የሚሰብኩትን ነው[6]::

*የነገረ መለኮት ሊቃውንት ኑፋቄ ወይም መናፍቅ ለሚለው ቃል የሚሰጡት ትርጒም ለየቅል ቢሆንም አብዛኞቹ የሚስማሙበት፣ «ከክርስትና እምነት የወጡ መናፍቃን ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ፤ በመሪዎቻቸው ወይም በድርጅቶቻቸው የተሰጠውን የተወሰነ አስተም ህሮአዊ ሥርዐት የሚከተሉ፤ ይህም አስተምህሮአዊ ሥርዐት ከሥልሳ ስድስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳን ጸሐፎች የተቀዳውን የክርስትና እምነት መሠረታዊ አስተምህሮ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ትምህርት የሚክዱትን መናፍቃን ብለን እንጠራቸዋለን»[7] የሚለውን ነው::*

## *ሐ. የነገረ መለኮት አጠቃቀሙ ትንታኔ*

በዚህ መጽሐፍ ኑፋቄ የሚለውን ቃል የምንጠቀመው በቋንቋዊ ፍቺው ሳይሆን፣ በነገረ መለኮታዊ አጠቃቀሙ ስለሆነ፣ ትንታኔው ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የትንታኔው ቃል ወይም ሐረግ ምን ዐይነት ትርጒም ወክሎ እንደሚገኝ ወደ መመልከቱ እንዝለቅ:-

1. « *ከክርስትና እምነት የወጡ መናፍቃን . . .*»

መናፍቃን በአስተምህሮ ምክንያት እውነተኛ ከሆነችው ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸው አፈንግጠው የወጡ ናቸው:: ይህም፣ መናፍቃን

---

[6] Bryan Wilson, "Sect" in The Westminster Dictionary of Christian Treology, ed. Alan Richardson and John Bowden (Philadelphia :Westminster, 1983) ገጽ 532::

[7] Gomes ገጽ 7

በቀደምትነት ከተመሠረተው እምነት ያፈነገጡ መሆናቸውን ይገልጻል:: እኛ አሁን የምንነጋገረው ከክርስትና እምነት ስለወጡት መናፍቃን ቢሆንም እንኳ፣ በሌሎች ሃይማኖቶችም ውስጥ መናፍቃን ይከሠታሉ:: ለምሳሌ በእስልምና ውስጥ ሱፊዎችና ጥቁር ሙስሊሞች [የእስላም ሕዝብ (Nation of Islam) በመባል ይታወቃሉ] የእስልምና ሃይማኖት መናፍቃን በመባል ይታወቃሉ:: እነዚህ እንቅስቃሴዎች ወይም ኅብረቶች ራሳቸውን ሙስሊም እያሉ ቢጠሩም እንኳ፣ ከመሠረታዊው የእስልምና ትምህርት የራቁ ናቸው::

«ከክርስትና እምነት የወጡ መናፍቃን» የሚለውን ሐረግ የተጠቀምንበት ዋነኛ ምክንያት፣ ብዙ ሰዎች መናፍቃን የሚለውን ቃል የሚጠቀሙት እንደ እስልምና ባሃኢዝም ወዘተ ያሉትን ሃይማኖቶች በሚያመለክት መልኩ ስለሆነ እንዲሁም፣ «የክርስትና እምነት መናፍቃን» የሚለው ሐረግ በክርስትናና በመናፍቃን መካከል ጕልሕ የሆነ ልዩነት መኖሩን ለማመልከት ነው::

## *2. « . . . ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ. . .»*

መናፍቃንን መናፍቃን ከሚያሰኛቸው መስፈርቶች ውስጥ፣ «ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ» የሚለው አንደኛው ነው:: ምንም እንኳ እስልምና ከክርስትና ጋር የሚቃረን እጅግ በርካታ ትምህርት ቢኖረውም፣ ራሱን ክርስቲያን ብሎ ስለማይጠራ በመናፍቃን ጐራ ሊፈረጅ አይችልም:: እስልምና ራሱን የቻለ፣ ከክርስትና እምነት ጋር የሰማይና የምድር ያህል የተራራቀ የዓለማችን ሃይማኖት ነው::

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን፣ የይሖዋ ምስክሮችና የእምነት እንቅስቃሴ ግን፣ «ከክርስትና እምነት የወጡ መናፍቃን» ብለን ልንጠ ራቸው



እንችላለን፤ ምክንያቱም ራሳቸውን ክርስቲያን እንዲያውም በምድር ላይ እነርሱ ብቻ ብቸኛ ክርስቲያኖች እንደሆኑ ስለሚያውጁ ነው::

ወንጌልን የሚቃወም ማንኛውም ሥርዐተ እምነትና ንጽሮተ ዓለም፣ ሰዎችን በመጽሐፍ ቅዱስ ራሱን የገለጠውን አምላክ ስለሚያርቃቸው ስሕተት ነው:: ነገር ግን ክርስቲያን ነን እያሉ መሠረታዊውን የክርስትና እምነት የሚቃወሙትን ብቻ መናፍቃን እንላቸዋለን::

## *3. « . . . በመሪዎቻቸው ወይም በድርጅቶቻቸው የተሰጠውን የተወሰነ አስተምህሮአዊ ሥርዐት የሚከተሉ. . .»*

አንዳንድ የመናፍቃን ድርጅቶችና እንቅስቃሴዎች ለምሳሌ የእምነት እንቅስቃሴ፣ የእግዚአብሔር ልጆች፣ የዩኒፊኬሽን ቤተ ክርስቲያን የተወሰኑ «ነቢያቶቻቸውን» «ባለ ሥልጣን ነቢያት» ናቸው በማለት የእውነት ምንጭ አድርገው ይቀበሏቸዋል::

አንዳንድ የመናፍቃን ድርጅቶች ደግሞ እውነትን የማግኘትና ሰዎችን በእውነት የመምራት ሥልጣን የድርጅቶቹ ብቻ እንደሆነ ይታመናል:: ለምሳሌ የይሖዋ ምስክሮች የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በመባል የሚታወቀውን ድርጅት የሚመሩት የአመራር አካላት («ልባምና ታማኝ ባሪያ» በመባል ይታወቃሉ) ወቅታዊ የሆነውን መንፈሳዊ ምግብ ያወርዳሉ» ተብሉ ስለሚታመን ለድርጅቱ አመራር አካላት ትምህርት፣ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይገዛሉ::

### *4.« . . . ይህም አስተምህሮአዊ ሥርዐት ከሥልሳ ስድስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳን ጸሐፊዎች የተቀዳውን. . . »*

ክርስቲያናዊ ትምህርት መመሥረት ያለበት፣ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል በሆኑት በሥልሳ ስድስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳን ጸሐፊዎች ብቻ ነው:: አንዳንድ መናፍቃን በእነዚህ መጻሕፍት ላይ መጻሕፍትን ይጨምራሉ፤ ይህ ጉዳይ እነርሱ ከጨመሩት መጻሕፍት ውጪ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በቂ እንዳልሆነ ወይም የእነርሱ መጻሕፍት መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚተኩ ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እንደሚስተካከሉ ማመናቸው ብቻ ሳይሆን፣ እነዚህ መጻሕፍት የቃለ እግዚአብሔርን ትምህርት በቀጥታ ስለሚቃረኑም ጭምር ነው::

### *5. «. . .የክርስትና እምነት መሠረታዊ አስተምህሮ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ትምህርት የሚክዱትን. . . »*

የክርስትና እምነት መሠረታዊ አስተምህሮ የሚባሉት፣ ክርስ ትናን ክርስትና የሚያሰኙት ትምህርቶች ናቸው:: ለዚህም ነው ዋለተር ማርቲን፣ «በአጭሩ ኑፋቄ ማለት፣ ርቱዕ ከሆነው የክርስትና አስተምህሮ ዐበይት ትምህርቶችን የሚክድ ማለት ነው»[8] የሚለው:: መሠረታዊ የሚባሉት ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች የእምነቱ ጽኑ አዕማድ ናቸው:: እነዚህም አስተምህሮዎች ትምህርተ ሥላሴ፣ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆኑን፣ ክርስቶስ በአካል ሥጋ ከሙታን እንደ ተነሣ፣ ምዕመናንም እንደዚሁ ከሙታን የሚነሡ መሆናቸውን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የፈጸመው ፀደኅንነት ሥራና ደኅንነት በጸጋ በእምነት በኩል መሆኑ ናቸው:: እነዚህ የክርስትና መሠረታዊ

---

[8] . Walter R. Martin, <u>Rise of the Cults</u> ( Santa Ana, Calif.: Vision House, 1977) ገጽ11::



ባሕርያት ናቸው:: ከእነዚህም መሠረተ እምነቶች ማፈንገጥ መናፍቅነት ነው:: እነዚህ አስተምህሮዎች ክርስትና ያረፈበት ዐለት መሆናቸውን ቃለ እግዚአብሔር ያስተምረናል (ማቴ 28÷19፤ ዮሐ 8÷24፤ 1ቆሮ 15፤ ኤፌ 2÷8-10) :: እነዚህን መሠረተ እምነቶች ክዶ የዘላለም ሕይወትን ማሰብ አይቻልም::

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች መሠረታዊ የሆነውን ክርስቲያን አስተምህሮ ከደቃቅ (ከንዑስ) ትምህርቶች ጋር ይቀይጡታል፤ ነገር ግን ይህ ስሕተት ነው:: ለምሳሌ አንድ ሰው፣ «በወህኒ የነበሩ ነፍሳት» (1ጴጥ 3÷19) ማን እንደሆኑ በሚሰጠው ገለጻ ሊሳሳት ይችላል፤ ወይም ንጥቀት መቼ ሊሆን እንደሚችል የጊዜ ሰሌዳ ሊያበጅ ይችላል:: ይህ ግን ትልቅ ስሕተት አይደለም፤ ልንታገሠው እንችላለን:: ነገር ግን አንድ ሰው ደኅንነት በጸጋ መሆኑን ወይም ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆኑን መካድ መሠረታዊ ችግር ነው፤ መናፍቅነት ነው፤ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን ጸንታ ከቆመችበት መሠረት አፈንግጦአልና ይህን ኑፋቄ እንለዋለን::

መሠረታዊ በሆኑ ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፣ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንና ፕሮቴስታንቶች (የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት) አንድ ዐይነት አቋም አላቸው:: ምናልባት አብያተ ክርስቲያት ያላቸውን መሠረተ እምነት አማኒያኖቹ ላይረዱት ይችላሉ:: እንዲረዱት ማድረግ ተገቢ ቢሆንም፣ ቤተ ክርስቲያኖቹን እንደ መናፍቅ መቍጠር ግን ፍጹም ስሕተት ነው:: እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት እርስ በርስ መነቃቀፋቸውንና አንዱ ሌላውን እንደ መናፍቅ መቍጠራቸው ትክክል አይደለም::

መሠረታዊ ከሆኑት የክርስትና አስተምህሮዎች አንዱን እንኳ መካድ በመናፍቃን ጐራ ለመፈረጅ በቂ ነው:: አብዛኞቹ መናፍቃን

ግን መሠረታዊ ከሆነው ከክርስትና አስተምህሮ አንድና ከዚያም በላይ ትምህርት የሚያጕድሉ (የሚክዱ) ናቸው:: ይህ የሚሆንበት ዋነኛው ምክንያት አንዱ አስተምህሮ ከሌላው ጋር የተቈራኘ በመሆኑ ነው::

አንዳንድ መናፍቃን መሠረታዊ የሆኑትን አስተምህሮዎች በይፋ ሲክዱ (ለምሳሌ የይሖዋ ምስክሮች:- ትምህርተ ሥላሴን፣ የክርስቶስን አምላክነት፣ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊ ህልውና [መንፈስ ቅዱስ ከአብ ጋር ትክክል እሪና ያለውና በአለመንበር መሆኑን]) አንዳንዶች ደግሞ ከሕደታቸው ስውር በሆነ ሁኔታ ነው:: ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የእምነት እንቅስቃሴ ነው፤ እንቅስቃሴው መጽሐፍ ቅዱሳዊና የቤተ ክርስቲያን ቃላትን ይጠቀማል፤ ነገር ግን ለቃላቱ የሚሰጠው ትንታኔ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም:: እንደዚህ እንቅስቃሴ ዳግም መወለድ ማለት አምላክ መሆን ወይም የአምላክን ባሕርይ ገንዘብ ማድረግ (መውሰድ) ማለት ነው::



# ክፍል ሦስት

# በመናፍቃን ተዘውትረው የሚታዩት ባሕርያት የትኞቹ ናቸው

## ሀ. የመናፍቃን አስተምህሮአዊ ባሕርይ[1]

በዚህ ክፍል ለማየት የምንሞክረው፣ የመናፍቃንን አስተምህሮአዊ ባሕርይ ነው:: የመናፍቃንን አስተምህሮአዊ ባሕርይ በመመርመር፣ የትምህርታቸውን ስሕተት እንዴት አድርገን ማወቅ እንደምንችል ለማየት እንሞክራለን:: ከፀሐይ በታች ያሉትን የክርስትና መናፍቃን ሁሉ አጥንተን አንዘልቅም፤ ነገር ግን የመናፍቃኑን ተመሳሳይ አስተምህሮአዊ ባሕርያት ማወቅ፣ በብዙ ጐኑ ጠቀሜታው ታላቅ ነው:: ስለዚህ በዚህ ክፍል ለማየት የምንሞክረው ልምምዳቸውን ሳይሆን የትምህርተ መለኮት አቋማቸውን ነው::

የመናፍቃንን አስተምህሮአዊ ባሕርይ ስናጠና፣ ሁሉም መናፍቃን ሁሉንም ባሕርያት ይጋራሉ ማለት ግን አይደለም:: ነገር ግን ባሕርያቱን በተወሰነ መጠን ስለሚጋሩ በመናፍቃን ጐራ ተፈርጀዋል:: ምክንያቱም እነዚህ ባሕርያት መሠረታዊ ልዩነት ይፈጥራሉና ነው::

መናፍቃን፣ መናፍቃን የተባሉት ከመሠረታዊው የክርስትና አስተምህሮ ስላፈነገጡ፣ አስተምህሮውንም ፊት ለፊት ስለተቃወሙ

[1] ይህ ክፍል በብዛት የተወሰደው ተስፋዬ ሮበሌ የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን (ራእይ አሳታሚ ድርጅት፤አዲስ አበባ 1991) ገጽ 7 ላይ ነው::

ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች ከመሠረታዊ እምነታቸው ይልቅ ለልም ምዳቸው ትኩረት ይሰጣሉ። እንዲሁም አንዳንድ ክርስቲያናዊ ተቋሞች የተሳሳተ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ዘዴን ይከተላሉ። ይህ አካሄዳቸው መሠረታዊውን የክርስትና ትምህርት እስካልተቃረነ ድረስ ሰዎቹን መናፍቅ ሊያሰኛቸው አይችልም።

## ለ. ተመሳሳይ የሆኑት የመናፍቃን አስተምህሮአዊ ባሕርያት

### 1. አስተምህሮተ ሥላሴን መካድ

ርቱዕ ( ትክክልኛ) የሆነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ በአንዱ የእግዚአብሔር ባሕርያት ውስጥ ሦስት ዘላለማዊ አካላት ይኸውም አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አሉ ብሎ ያምናል። ምናልባት ሁሉም መናፍቃን የሥላሴን አስተምህሮ ይክዳሉ ቢባል ስሕተት አይሆንም። አንዳንድ መናፍቃን የሥላሴን አስተምህሮ ከአረማውያን የመድበለ አማልክት አስተሳሰብ ጋር ሲያመሳስሉት፣ አንዳንዶች ደግሞ አስተም ህሮውን እንደሚቀበሉ ያውጃሉ፤ ነገር ግን አስተምህሮውን የሚያብ ራሩበት መንገድ ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት እጅግ የራቀ ነው።

### አሰረጅ

ከምሥረታው ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን የሥላሴን አስተምህሮ በቀጥታ የሚቃወመው የይሖዋ ምስክሮች ደርጅት ነው[2]። እንደ

[2] ድርጅቱ፣ «በሥላሴ ማመን ይገባሃልን?» በሚል ርእስ ላዘጋጀው ጽሑፍ ተስፋዬ ሮበሌ በሥላሴ ማመን አይገባህምን? በሚል ርእስ የሰጠውን ምላሽ ይመለከቱ።



ድርጅቱ አስተምህሮ፣ የሥላሴ ትምህርት አረማውያን በክርስትና እምነት የጣሉት አሻራ እንደሆነ ይገልጻል[3]።

የሥላሴን አስተምህሮ ከሚክዱ መናፍቃዊ ድርጅቶች መኻል «የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን» አንደኛው ነው። እንደ ድርጅቱ አስተምህሮ እግዚአብሔር፣ አብ፣ አምላክ፣ ክርስቶስ የሚባለው አንዱና ብቸኛው አምላክ ሲሆን፣ ኢየሱስ፣ ወልድ፣ ልጅ ወዘተ የሚባለው ደግሞ እግዚአብሔር አብ ያደረበት ሰው ብቻ ነው። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የአብ ሌላው ስም ነው። እንደ ድርጅቱ ትምህርት ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ጌታ ኢየሱስ ማለት አብና ወልድ ማለት ነው። ኢየሱስ አምላክ ሳይሆን አምላክ የሚኖርበት (ያደረበት) ሰው ነው።

ሞርሞኖች የሥላሴን አስተምህሮ እንደሚያምኑ ይገልጻሉ፤ ነገር ግን ትምህርቱን ሦስት አምላክ አድርገው ያቀርቡታል። እንደ ድርጅቱ ትምህርት ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል አንዱ የሆነው ጀምስ ታልማግ፣ «አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሚች እንደሆኑት ሰብአዊ ፍጡራን የተለያዩ አካላት ናቸው» ይላል[4]። ድርጅቱ በሥላሴ አካላት መካከል ያለው አንድነት የዐላማና የስምምነት ብቻ እንደሆነ ይገለጻል[5]።

ሜሪ ቤከር ኤዲ የምትባለው አሜሪካዊት ወይዘሮ የመሠረተችውና « ክርስቲያን ሳይንስ » በመባል የሚታወቀው መናፍቃዊ ድርጅት፣ የክርስቶስን አምላክነት በመካድ የሥላሴን አስተምህሮ ይቃወማል። ወይዘሮዋ፣ «ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ

[3] «በሥላሴ ማመን ይገባሃልን» (ኒውዮርክ፤ የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር 1989) ገጽ 8-12 ።

[4] Gomes ገጽ 25 ከ James Talmage, A Study of Articles of Faith ( Salt Lake City: The Church of Jesus Christ of Latter-day Saints, 1976), አንቀጽ 1 ገጽ 29-51 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[5] ዝኒ ከማሁ።

አይደለም፤ ነገር ግን እርሱ ራሱ እንዳስተማረው የእግዚአብሔር ልጅ ነው»[6] ትላለች::

## 2. ደኅንነት በእምነት አማካይነት በጸጋ መሆኑን ይክዳሉ

ቫን ባለን እንደሚለው የሁሉም መናፍቃን ትምህርታቸው ማእከል ያደረገው፣ «ራስህን ማዳን አለብህ» በሚለው አስተምህሮ ላይ ነው[7]:: ለእግዚአብሔር ጸጋ የከንፈር አገልግሎት ብቻ እንዲሰጡ ያደረጋቸው፣ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ያከናወነውን (የፈጸመውን) የደኅንነት ሥራ ስለሚያቃልሉ ነው:: የክርስቶስ የደኅንነት ሥራ በራሱ ሙሉ በሙሉ የማያድን ከሆነ፣ የጐደለውን በሥራ ማካካስ ወይም መሙላት አይቀሬ ነው::

አንዳንድ መናፍቃን የክርስቶስ የማዳን ሥራ፣ አንድ ሰው ወደ እምነት ከመምጣቱ በፊት ያለበትን ኀጢአት የማጠብ ኀይል አለው:: ነገር ግን ወደ እምነት ከመጣ በኋላ ራሱን ማዳን ያለበት እርሱ ራሱ ወይም የእርሱ ድርጅት ወይም ደግሞ የድርጅቶቹ የአመራር አካላት በሚሠሩት ሥራ እንደሆነ አጠንክረው ያስተምራሉ:: አንዳንዶች ደግሞ፣ የክርስቶስን የማዳን ሥራ ትንንሽ ኀጢአቶችን ብቻ እንጂ፣ ትልልቅ ኀጢአቶችን እንደማይጨምር ይገልጻሉ:: የተቀሩት ደግሞ የክርስቶስ የደኅንነት ሥራ ለሰው ልጆች ሁሉ እንደማይሆን፣ ነገር ግን እርሱ የጀመረውን ሥራ እነርሱ ከዳር እንደሚያደርሱት ያውጃሉ::

[6] Gomes ገጽ 26 ከMary Baker Eddy. Science and Health with Key to the Scriptures ( Boston Trustees Under the Will Mary Baker G. Eddy,1934) ገጽ 361 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::



## አስረጅ

ለይሖዋ ምስክሮች፣ ደኅንነት ለመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ሙሉ በሙሉ ከመገዛትና በሚያወጣቸውም ፕሮግራሞች ተካፋይ ከመሆን ውጪ የሚታሰብ አይደለም[8]::

እንደ ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ደግሞ ደኅንነት የሚገኘው፣ የድርጅቱ አባል በመሆን፣ በትክክለኛው የጥምቀት ቀመር በመጠመቅ[9] እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በሆነው ልሳን በመናገር ነው::

እንደ ሞርሞኖች ደግሞ አንድ ሰው ደኅንነትን ማሰብ ያለበት፣ አምኖ ንስሓ ከገባ በኋላ የመንፈስ ቅዱስን ለመቀበል ስጦታ እጅ ተጭኖ ከተጸለየለት በኋላ ነው[10]::

ዴቪድ ኮረሽ የተባለው መናፍቅ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራው ሕያው የሚሆነው፣ እስከ 31 ዓ.ም ብቻ እንደሆነ ገልጾአል:: ስለዚህ ከ31 ዓ.ም. በኋላ ላለው የሰው ልጆች ኀጢአት መሞት እንዳለበት ይገልጽ ነበር[11]::

ጥር 6 ቀን 1920 ዓ.ም በኮርያ የተወለደውና በኮርያ ተራራ ሥር፣ ከራሱ ከክርስቶስ ራእይ ተቀብያለሁ የሚለው ሳን ማዮንግ ሙን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የአካልና የመንፈስ ደኅንነት ማምጣት ስላልቻለ ይህን ነገር ከዳር እንዲያደርስ እርሱ እንደተመረጠ፣ ይህንም ያበሠረው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ይገልጻል[12]:: ኢየሱስ ክርስቶስ ሊፈጽም

8. ተስፋዬ ሮበሌ የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን (ራእይ አሳታሚ ድርጅት፤ አዲስ አበባ 1991 ) ገጽ 104-122 ይመለከቷል::

9. እንደ ድርጅቱ አስተምህሮ ትክክለኛው የጥምቀት ቀመር በኢየሱስ ክርስቶስ ስም» ነው፤ ይህም ደኅንነት መሠረት ነው::

10. Gomes ገጽ 27 ከ Talmage. A Study of the Articles of Faith. አንቀጽ 4 ገጽ 107-108 ላይ ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

11. ዝኒ ከማሁ ከ Samples etal., Prophets of the Apocalypse ገጽ 205 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

12. ዝኒ ከማሁ ገጽ 28:: ከ Sun Myung Moon, Divine Principle ( Washington, D.C HSAUWC), ገጽ 147 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

የቻለው መንፈሳዊውን ደኅንነት ብቻ ሲሆን፣ ሙን ደግሞ አካላዊውን ደኅንነት እንዲያመጣ ተመርጦአል።

## 3. የአካል ትንሣኤ ይክዳሉ

የክርስቶስ የአካል ትንሣኤ የክርስትና እምነት ያረፈበት ታሪካዊ መሠረት ነው (1ቆሮ 15)። መናፍቃን ደግሞ መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ማጣመም ተቀዳሚ ተግባራቸው ነው። በስፋት የታወቀውና የትንሣኤን አስተምህሮ የሚያጣምመው ትምህርት፣ ትንሣኤን መንፈሳዊ የሚያደርገው አስተምህሮ ነው። እንደ ዚህ ትምህርት፣ ክርስቶስ ከሙታን የተነሣው ረቂቅ መንፈስ ሆኖ ነው። ለዚህ ክሕደት ጥሩ አስረጅ የሚሆኑት የይሖዋ ምስክሮች ናቸው። እንደ መጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር፣ «ንጉሥ ክርስቶስ ኢየሱስ በሥጋ ሞቶ፣ የማይታይ ፍጥረት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል»[13]። ይህ ብቻ አይደለም የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት፣ የክርስቶስን ትንሣኤ አስመልክቶ እንዲህም የሚል ግምት አለው፣ «የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ወደ ጋዝነት ተለውጦአል፤ ወይም ለእግዚአብሔር ፍቅር ታላቅ መታሰቢያነት በአንድ ስፍራ ተጠብቆ ነው ያለው»[14]። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቶስ በሥጋው ከሙታን የተነሣ መሆኑን በግልጽ ይናገራል[15]።

## 4. መጽሐፍ ቅዱስ ፍጹም ሥልጣን ያለው መሆኑን ይክዳሉ

አንዳንድ መናፍቃን መጽሐፍ ቅዱስ በስሕተት እንደ ተሞላ ይናገራሉ። አንዳንዶች ደግሞ ሥልጣናዊ ቃልነቱን በመቀነስ፣

[13] Let God Be True (1946) ገጽ 22

[14] Studies in the Scripture ገጽ 129 ቅጽ 2

15 « የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ» የሚለውን ርእስ ይመለከቷል።



« አሮጌው ብርሃን» በማለት ይጠሩታል። ይህም፣ «አዲሱ ብርሃን» ከሚሉት ከእነርሱ አስተምህሮ ማነሱን ያመለክታል።

ሌሎች ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል እንደሆነ ቢናገሩም፣ መጽሐፍ ቅዱስን «የሚተረጒሙት» ከራሳቸው አስተምህሮ ጋር እንዲስማማ አድርገው ነው።

አንዳንዶች ደግሞ ቃለ እግዚአብሔርን የሚያቃልሉት ከእነርሱ አስተምህሮ ጋር የሚስማሙ ሌሎች ጽሑፎችን በማዘጋጀት ነው፤ እነዚህ ጽሑፎች ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ ይታያሉ።

## አስረጅ

የይሖዋ ምስክሮች መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል እንደሆነ፣ የአስተምህሮና የሥነ ምግባር መሠረት እንደሆነ ይገልጻሉ፤ ነገር ግን ከድርጅቱ አስተምህሮ ጋር እንዲጣጣም ተደርጐ የተዘጋጀው መጽሐፍ [የአዲሲቱ ዓለም ትርጒም] ድርጅቱ በተደጋጋሚነት የሚያውጀውን ዐዋጅ ከልብ እንዳልተቀበለው የሚገልጽ ነው። የአዲሲቱ ዓለም ትርጒም ያለምንም ቃለ እግዚአብሔርና የታሪክ ማስረጃ ያህዌ ( ጆሆቫ) የሚለውን ስም በአዲስ ኪዳን ንባባት ውስጥ 237 ጊዜ በላይ መጠቀሙ፣ ድርጅቱ ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነትና የሥላሴን አስተምህሮ ለመቃወም ምን ያህል እንደ ጠቀመው፣ ቃሉን በተጠቀሙባቸው ቦታዎች ሁሉ በግልጽ መረዳት ይቻላል።

የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን መሥራች የሆነው ዮሴፍ ስሚዝ፣ በዘፍጥረት ምዕራፍ 50 ላይ የእርሱን መምጣት የሚገልጽ «ትንቢት» ይሆን ዘንድ 14 ቊጥሮችን ጨምሮበታል። የሞርሞኖች የእምነት አንቀጽ፣ «መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል ከተተረጐመ፣ የእግዚአብሔር ቃል

ነው፤ እንዲሁም የሞርሞኖች መጽሐፍ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ እናምናለን»[16]ይላል:: ይህ ብቻ አይደለም ዋልተር ማርቲን፣ መጽሐፍ ቅዱስ የሞርሞኖችን መጽሐፍ በተቃወመበት ቦታ ሁሉ፣ እንዲጣጣም ተደርጐ ይተረጐማል» ይለናል:: ይህ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ከሞርሞኖች መጽሐፍ ጋር እንኳ እኩል እንደማይታይ ያስረዳል:: ሞርሞኖች ቃለ እግዚአብሔርን የሚያዋርዱት ከመጽሐፍ ቅዱስ እኩል የሚታይ መጽሐፍ በመጨመር፣ ከእነርሱ መጽሐፍ ጋር በማይታረቅበት ቦታ ሁሉ እንዲታረቅ ተደርጐ እንዲተረጐም ብቻ ሳይሆን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጨማሪ ቍጥርና ምዕራፍ በመጨመርም ነው::

## 5. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ መንገድ መተርጐም

አብዛኛውን ጊዜ መናፍቃን ለክርስቲያናዊ ቃላት አዲስ ትርጓሜ መስጠት ይወዳሉ:: ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ በ2ቆሮ 11÷4 ላይ ሐዋርያት ከሰበኩት የተለየ (ገላ1÷6-9) ሌላ ክርስቶስ፣ ሌላ መንፈስ፣ ሌላ ወንጌል የሚለውን አጠቃቀም ሲጠቀም የሚስተዋለው:: መናፍቃን ስለ ክርስቶስ፣ ስለ ወንጌል፣ ስለ ደኅንነት ወዘተ አብዝተው ይናገራሉ፤ ነገር ግን ቃሉን የሚጠቀሙበት መጽሐፍ ቅዱስ ቃሉን በተጠቀመበት መንገድ አይደለም:: ዋልተር ማርቲን እንደሚለው፣ «ብዙውን ጊዜ ከመናፍቃን ጋር የምናደርገው ውይይት ፍሬ አልባ የሚሆነው፣ ለምንወያይባቸው ጕዳዮች ትክክለኛውን ትርጕም (ገለጻ) ባለመስጠታችንና እነርሱም ምን ማለታቸው እንደሆነ እንዲገልጹልን ባለመጠየቃችን ነው»[17]:: ክርስቲያኖች ከመናፍቃን ጋር የሚያደርጉት ውይይት ስኬታማ የሚሆነው፣ መናፍቃኑ ቍልፍ የሆኑ ቃላትን

[16] Gomes ገጽ 30 ከArticles of Faith Artice 8 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::
[17] Martin, Kingdom of the Cults ገጽ 19::



እንዴት እንደሚመለከቷቸው አስቀድመው የሚያውቁ ከሆነ፣ አሊያም በውይይቱ ወቅት እንዲያብራሩላቸው በመጠየቅ ነው::

### አስረጅ

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አማኞች በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን ይላሉ:: እንደ ድርጅቱ አስተምህሮ አብ እግዚአብሔር፣ ወልድ ሰው* ብቻ፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የአብ ሌላው ስም ነው:: ስለዚህ አንድ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አባል በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ አምናለሁ ቢለን፣ ግለሰቡን በሥላሴ የምናል ልንለው ነው?

ይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን እናምናለን ይላሉ፤ ይህ ማለታቸው ግን ሰይጣን የዚህ ዓለም አምላክ፣ ሙሴ የፈርዖን አምላክ እንደተባለው ማለት እንጂ፣ እንደ አብ ሁሉን ቻይ አምላክ ማለት አይደለም ይላሉ:: ስለዚህ የይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስን አምላክ ቢሉ አምላክ ነው ስትሉ ምን ማለታችሁ ነው ብለን ልንጠይቃቸው ይገባል::

የእምነት እንቅስቃሴን አስተምህሮ የተቀበለ ሰው፣ «ዳግም ተወልደሃል» ብሎ ቢጠይቅ የእግዚአብሔር ልጅ ሆነሃል ማለቱ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ገንዘብ በማድረግ እግዚአብሔር ሆነሃል ማለቱ ነው::

## 6. ድርጅቶቻቸውና መሪዎቻቸው የእግዚአብሔር ብቸኛ እንደራሴዎች እንደሆኑ ይናገራሉ

የብዙ መናፍቃዊ ድርጅት መሪዎች፣ የእግዚአብሔር ብቸኛ ወኪሎች፣ ድርጅታቸውም በአምላክ የሚመራ ፍጹም ብቸኛ ድርጅት፣

* ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ማንኛውም ዘረ አዳም ሰው ነው የሚለውን ግእዙ «ዕሩቅ ብእሲ» ይለዋል፡

እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሚገናኝባቸው ድልድዮች፣ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ መገለጥ ተቀባዮች አድርገው ራሳቸውን ያቀርባሉ::

ነገር ግን ይህን የመናፍቃን ዐዋጅ ክርስቶስ፣ « እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» ከሚለው ወይም ሐዋርያት፣ «መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» (ሐሥ 4÷12) በማለት ኢየሱስ ክርስቶስን የእግዚአብሔር ብቸኛ እንደራሴ (ወኪል) ከማድረጋቸው ጋር ልናመሳስለው አይገባም:: ምክንያቱም ይህ የቃለ እግዚአብሔር እውነት ነው::

## አስረጅ

«የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር» በመባል የሚታወቀው የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት፣ የአምላክ ፍጹም ብቸኛ ድርጅት እንደሆነ ይገልጻል:: የድርጅቱ ሥልጣናዊ መዋቅር፣ «ታማኝና ልባም በሆኑ ባሮች» እንደተሞላ፣ እነዚህም ባሮች ወቅታዊ የሆነውን መንፈሳዊ ምግብ በወቅቱ እንደሚያወርዱ የእግዚአብሔር እንደራሴዎች ይታያሉ[18]:: ሁሉም የይሖዋ ምስክር ያለምንም ጥያቄና ቅድመ ሆኔታ ትምህርታቸውን መቀበልና መታዘዝ ይጠበቅበታል::

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን በመባል የሚታወቀው መናፍቃዊ ድርጅት፣ ሰዎች የዘላለምን ሕይወት የሚያገኙት፣ በእነርሱ ቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር ሲጠለሉ ብቻ እንደሆነ ያስተምራል::

18 You Can Live Forever in Paradise on Earth (1982) ገጽ 191-195



## 7. ከአስተምህሮአቸው ጋር የሚቃረኑ እውነቶችን ከቁብ አይቈጥሯቸውም

በርካታ መናፍቃን ከዐዋጃቸው ጋር የሚቃረኑ እውነቶችን ትኩረት አይሰጡአቸውም፤ ወይም አቃለው ይመለከቱአቸዋል::

## አስረጅ

የይሖዋ ምስክሮች ሲፈጸሙ (ወይም ብዙ እውነት ሲሆኑ) ያልታዩ የሐሰት ትንቢቶችን ተንብየዋል፤ ነገር ግን ይህንን አስተምህሮ እንዲገነቡ ያደረጋቸውን የትንቢት መጻሕፍትን የሚተረጒሙበትን ዘዴ አሁንም አልቀየሩም:: የአርማጌዶን ጦርነት በ1914 ዓ.ም. ይሆናል ተብሎ ነበር፤ በዚህ ወቅት ሊሆን ሳይችል በመቅረቱ ቀኑ ወደ 1915 ዓ.ም ከዚያም 1975 እና 1981 ዓ.ም. ተሸጋገረ[19]:: ነገር ግን ይህን መሰሉን ትንቢት የተናገረው ድርጅት አሁንም ራሱን ከአምላክ እውነተኛ ትንቢት ተቀባይ አድርጎ ይቈጥራል::

ሞርሞኖች «የሞርሞን መጽሐፍ» የተባለውን መጽሐፋቸውን 3,913 ጊዜ ስሕተቱን አርመዋል[20]:: ነገር ግን አሁንም ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል፣ «በምድር ላይ ፍጹም ስሕተት የሌለበት መጽሐፍ»[21] ይባላል::

ክርስቲያን ሳይንስ የተባለውን መናፍቃዊ ድርጅት የመሠረተችው ሜሪ ቤከር ኤዲ፣ በሽታ እውነትነት የሌለው ሕልም (ቅዠት) ነው ብትልም፣ እርሷ ራሷ ታማ በዶክተር ትረዳ እንደ ነበር፣ የሕመም

19 የመጠበቂያ ግንብ (ሚያዚያ 1 ቀን 1972):: በወቅቱ የነበሩ ብዙ የይሖዋ ምስክሮች፣ በዚህ ምክንያት ድርጅቱን ለቀው ወጥተዋል::

20 Martin, Kingdom of the Cults ገጽ 29::

21 በ1991 ዓ.ም የታተመው « የሞርሞኖች መጽሐፍ» መግቢያ ላይ ጆሴፍ ስሚዝ ያሰፈረው ዐረፍተ ነገር ነው::

ማስታገሻ መርፌ እንደምትወጋ፣ አጥርታ እንድታይ የሚረዳት መነጽር ታደርግ እንደ ነበር፣ በሕመም ምክንያት ብዙ ጥርሶቿን እንዳጣች ይታወቃል[22]:: ነገር ግን ዛሬም የኤዲ ተከታዮች በሽታ እውነትነት የሌለው ቅዠት ነው ይላሉ[23]::

## 8. የዘላለምን ኩነኔ (ቅጣት) ይክዳሉ

ብዙ መናፍቃን የእግዚአብሔር ቃል ስለ ዘላለም ቅጣት የሚያስ ተምረውን እውነታ አይቀበሉም:: አንዳንዶች ለምሳሌ የሁለንታዊ ትምህርት አራማጆች፣ የሰው ልጆች ሁሉ የዘላለምን ሕይወት እንደ ሚያገኙ ሲያስተምሩ፤ ሌሎች ደግሞ፣ አምላክ ኀጢአተኞችን ወደ አለመኖር ደረጃ ይወስዳቸዋል [ብን ብለው እንዲጠፉ ያደርጋቸዋል] ይላሉ::

### አስረጅ

የይሖዋ ምስክሮች በድርጅት መልክ ተዋቅረው መንቀሳቀስ ከጀመሩ 120 ዓመት ይሆናቸዋል:: በእነዚህ ዘመናት ሁሉ ኀጢአተኞች ዘላለማዊ ቅጣት ይጠብቃቸዋል የሚለውን ትምህርት፣ አጥብቀው ሲቃወሙ ኖረዋል:: የድርጅቱ ሁለተኛ ፕሬዝዳንት የነበረው ጆሴፍ ፍራንክሊን ሮዘርፎርድ፣ «የዚህ [የዘላለም ቅጣት] እግዚአብሔርን የማያከብር አስተምህሮ ጠንሳሽ ሰይጣን ነው:: ይህንን ያደረገበትም ምክንያት፣ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዳያነቡ ለማስፈራራትና እግዚአብሔርን እንዲጠሉ ለማድረግ ነው»[24]ብሎአል::

---

[22]. Martin, Kingdom of Cults ገጽ 29::
[23] ዝኒ ከማሁ::
[24] Rutherford, Let God Be True ገጽ 79:: በቅንፍ ያለውን አይጨምርም:: ይህን ትምህርት አስመልክቶ ያለውን የድርጅቱን ትምህርት ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር ገጽ 98-100፣ 168-175፤ 375-379፤ 382-383 እንዲሁም You Can Live Forever in Paradise on Earth ገጽ 76-89 ይመልከቱ::ይህን ርእስ ጉዳይ ተስፋዬ ሮበሌ የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን ገጽ 123-132 በተሰኘው መጽሐፍ ላይ በስፋት መርምሮታል::



ዩኒቴሪያን ዩኒቨርሳሊስት የተባለው መናፍቃዊ ድርጅት የሥላሴን አስተምህሮ ብቻ ሳይሆን፣ የዘላለም ኩነኔንም ቅጣት ይቃወማል:: እንዲያውም የድርጅቱ መሠረተ እምነት ሰው ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዳለው ይገልጻል[25]::

## 9. ከአስተምህሮአቸው ይልቅ ለልምምዳቸው ትኩረት ይሰጣሉ

አንዳንድ መናፍቃን ከእውነትና ከምክንያታዊ አስተሳሰብ ይልቅ፣ ለስሜት ከፍተኛ ቦታ ይሰጣሉ:: በዚህ መሰሉ የመናፍቃን እንቅስቃሴ ውስጥ ያሉ ሰዎች፣ አስተምህሮአችን ከእግዚአብሔር ቃል የመነጨ ነው ወይ? ለሚለው ጥያቄ ሳይሆን ጥሩ ስሜት ተሰምቶኛል ወይ? ከቀድሞ ልምምዴ ጋርስ ይስማማል ወይ? ለሚለው ትልቅ ትኩረት ይሰጣሉ:: ስሜትና የግል ልምምድ መጥፎ ነው ለማለት አይደለም:: ነገር ግን ስሜትም ሆነ ልምምድ ተገቢ የሆነውን ስፍራ መያዝ አለባቸው:: የእግዚአብሔር ቃል፣ « እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህ [mind] ውደድ» ይላል ( ዘዳ 6፥5፤ ማቴ 22፥37፤ ማር 12፥30፤ ሉቃ 10፥27):: ይህ ዐይነቱም አምልኮ እውነትን ከስሜት ጋር አጣምሮ የያዘ ነው:: የክርስትና፣ እውነት የተመሠረተው በእውነታዎች ላይ እንጂ፣ በስሜት ላይ እንዳልሆነ አጠንክሮ ያምናል::

### አስረጅ

ብዙ ክርስቲያኖችን በማሳሳት ላይ የሚገኘው የእምነት እንቅ ስቃሴ ትምህርት ዕውቀትን የስሜት ዕውቀትና የመገለጥ ዕውቀት ብሎ በመክፈል፣ ሃይማኖታዊ እውነታዎች በአምስቱ የስሜት ሕዋሳቶቻችን

---

25 Mather and Nichols, Dictionary ገጽ 286::

የምንገበያቸው ሳይሆኑ፣ በመገለጥ ብቻ የምናውቃቸው እንደሆኑ ያስተምራል:: እንዲያውም ወደ መገለጥ ዕውቀት ለመግባት በስሜት ሕዋሳቶቻችን የሚታወቁትን እውነታዎች መካድ እንደሚያስፈልግ አጠንክሮ ያስረዳል:: እንደዚህ እንቅስቃሴ ትምህርት ከሆነ፣ የስሜት ሕዋሳቶቻችንንም ሆነ አእምሮአችንን መጠቀም ሥጋዊነት ነው፤ የእግዚአብሔር እውነት በአእምሮና በስሜት ሕዋስ ፈጽሞ አይታወቅም ባይ ነው:: ከዚህ የተነሣም ክርስቲያናዊ እውነቶችን በቃለ እግዚአብሔር መመርመር አይፈ ቅድም[26]:: በእንቅስቃሴው ተከታዮች ዘንድ እንደ ትልቅ የእግዚአብሔር ሰው የሚቈጠሩት ኬኔት ሐጌን፣ አትተች፤ ግን «እግዚአብሔር እንዲገ ልጥልህ ጸልይ»[27] የሚለው አነጋገራቸው በጽሑፋቸው ተደጋግሞ የሚዘወተረው፣ መንፈሳዊ እውነትን በአእምሮአችን መረዳት አንችልም ስለሚሉ ነው::

ሞርሞኖች፣ « . . . መጻሕፍትንም ሲከፍትልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን» (ሉቃ 24÷32) የሚለውን ጥቅስ በመጥቀስ፣ እውነት እውነት መሆኑ የሚረጋገጠው፣ «ልባችን የሚቃጠልብን» ከሆነ ብቻ ነው ይላሉ:: ለሞርሞኖች የእውነት መመዘኛው ሚዛን «የልብ መቃጠል» ነው::

## *10. ከእግዚአብሔር በቀጥታ ተቀብለናቸዋል ለሚሏቸው መገለጦችና ራእዮች ከፍተኛ ትኵረት ይሰጣሉ*

መናፍቃን በተለይም የእንቅስቃሴው መሪዎች ከእግዚአብሔር ጋር አለን ከሚሉት ቀጥተኛ ግንኙነት የተነሣ፣ ራእይና መገለጥ እንደሚወርድላቸው እንዲሁም እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚሆነውን

[26] Kenneth Hagin, I Believe in Visions (Old Tappan N.J. : Fleming H.Revell, 1972)
[27] Kenneth Hagin, The Voice of Healing (Apr. 1963).



መንፈሳዊ ምግብ የሚሰጠው በእነርሱ በኩል ብቻ እንደሆነ ይገልጻሉ:: አብዛኛውን ጊዜ መገለጦቻቸውና ራእዮቻቸው የሚያተኵሩት የመጨረሻውን ዘመን በተመለከተ ሲሆን፣ የእነርሱ ዕጣ ፈንታም ምን እንደሆነ፣ ከራእዩና ከትንቢቱ ጋር ተያይዞ ይቀርባል:: ቃለ እግዚአብሔር፣ «ሁሉንም መርምሩ፤ መልካሙን ያዙ» (1ተሰ 5÷21) ይለናል፤ የተነገረው ትንቢት እንደተባለው ካልተፈጸመ ትንቢቱም ሆነ ነቢዩ ከእግዚአብሔር አይደሉም (ዘዳ 18÷22):: የአንድ ትንቢት ወይም መገለጥ ትክክለኛነት የሚረጋገጠው ትንቢቱ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በመስማማቱ ነው (ኢሳ 8÷20) ::

## *አስረጅ*

የሞርሞንን እምነት የመሠረተው ጆሴፍ ስሚዝ በ1820 ዓ.ም. ላይ እግዚአብሔር አብንና ወልድን በራእይ እንደተመለከተ ይገልጻል:: ስሚዝ በዚህ ራእይ ከየትኛውም ሃይማኖታዊ ድርጅት ጋር እንዳይገጥም ይነገረዋል:: ምክንያቱም፣ «ሁሉም የሃይማኖት ድርጅቶች የተሳሳቱ ስለሆኑ» እንዲሁም « የሃይማኖት መግለጫው ጸያፍ ስለሆነ ነው»[28]:: በመስከረም 21 ቀን 1823ዓ.ም ላይ ሞሮናይ የተባለ መልአክ እንደተገለጠለትና «ሞርሞን መጽሐፍ» ምን መሆን እንዳለበት የሚገልጽ የወርቅ ሳሕኖች እንደ ሰጠው ተናገረ:: ሞሮናይ የተባለው መልአክ በ1827ዓ.ም ዳግም ይገለጥለትና ሳሕኖቹን በመቈፈር የትርጕም ሥራ እንዲጀምር ፍቃድ ይሰጠዋል:: በወርኀ ግንቦት 1829ዓ.ም መጥምቁ ዮሐንስ ለስሚዝና ለኦሊቨር ኮድሪ ይገለጥላቸውና አሮናዊ ክህነት እንደተሰጣቸው ያረጋግጥላቸዋል[29]:: ጆሴፍ ስሚዝ ከሞተ በኋላ፣ ድርጅቱን የመምራት ኀላፊነት የተረከበውና «የሀሥራ

[28] Gomes ገጽ37 ከ Pearl of Great Price ( 1851, rev. ed, Salt Lake City: Church of Jesus Christ of Latter-day Saints, 1981) :19 ላይ ጠቅሶ እንደጻፈው ::
[29] መጽሐፍ ቅዱስ አሮናዊ ክህነት የተሰጣቸው ለሌዊ ልጆች ብቻ እንደሆነ ይነግረናል ( ዘፀ 4÷14፤29÷1):: እግዚአብሔር አምላክ ይሆን የክህነት አገልግሎት ለሌዊ ለጆች የሰጣቸው፣ የእስራኤል ልጆችን ወክለው ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ነው ( ዕብ 5÷1-3):: ከኢየሱስ ሞት በኋላ ሌዋዊም ሆነ አሮናዊ ክህነት አያስፈልግም፡

የሕዝቦች ቤተ መቅደስ የሚባለውን ድርጅት የቈረቈረው ጂሚ ጆንስ ኢንድያናፖሊስ የተባለው የአሜሪካን አካባቢ ሐምሌ 15 ቀን 1967 ዓ.ም. በኒውኩለር ጦርነት ያጠፋል የሚል ትንቢት አስተላልፎ ነበር[44]::

የእግዚአብሔር ልጆች [Children of God] የሚባለውን መናፍቃዊ ድርጅት ያስተዳድር የነበረው ሞስስ ዴቪዲ፣ ከሆቴክ የሚባል ጅራታማ ኮከብ በ1974 ዓ.ም. አሜሪካንን ያጠፋል የሚል ትንቢት ተንብዮ ነበር[45]::

## 13. የአማኞችን ክህነት ይክዳሉ

መጽሐፍ ቅዱስ ምዕመናን ሁሉ ካህናት መሆናቸውን ያስተምረናል (1ጴጥ 2÷4-10፤ ራእ 1÷6፤ 5÷10):: ይህም ማለት እያንዳንዱ አማኝ ያለምንም ሰብአዊም ሆነ መላእክት መካከለኛነት፣ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ብቻ፣ ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ መገናኘት ይችላል ማለት ነው (ዕብ 4÷16)::

በርካታ መናፍቃን፣ ተከታዮቻቸው ለድርጅቶቻቸውና ለመሪዎ ቻቸው ይገዙ ዘንድ፣ የአማኞችን የክህነት አገልግሎት በመካድ ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነት የሚረዱት በድርጅታቸው ወይም በአመራር አባላቱ ብቻ እንደሆነ ይገልጻሉ (1ዮሐ 2÷26-27)::

## አስረጅ

«የዳዊት ሥር» በመባል ይታወቅ የነበረው መናፍቃዊ እንቅስቃሴ መሥራች የነበረው ዴቪድ ኮርሽ፣ ለተከታዮቹ መጽሐፍ ቅዱስን ማብራራት (መተርጐም) የሚችለው እርሱ ብቻ እንደሆነ

[44] Gomes ገጽ 41 ከ Sparks, The Mindbenders ገጽ 263 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::
[45] ዝኒ ከማሁ:: Moses David, "40 Days and Nineveh Shall Be Destroyed" Tract published in 1973. ጠቅሶ እንደ ጻፈው::



ገልጾአል[46]:: የይሖዋ ምስክሮችን ድርጅት የመሠረተው ቻርልስ ታዝ ራስል «ስተዲስ ኢን ዘ ስክሪብቸርስ» በተባለው መጽሐፉ፣ «የተገነዘብነው ነገር ቢኖር፣ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ አንብበው መለኮታዊ ምሪትን ማግኘት እንደማይችሉ ነው:: ስክሪብቸር ስተዲስን መጠቀም ከጀመረ በኋላ ጥቂት ተጠቅሞባቸው፣ ተረድቶአቸው፣ ለዐሥር ዓመት እንኳ ካነበባቸው በኋላ የሚተዋቸውና ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ የሚመለስ ሰው፣ ከተሞክሮአችን የተረዳነው ነገር በሁለት ዓመት ውስጥ ወደ ጨለማ እንደሚሄድ ነው»[47] ብሎአል:: ድርጅቱ እስከ አሁን ድረስ መለኮታዊ እውነትን ለመረዳት፣ ለመጠበቂያ ግንብ ማኅበር መገዛት የግድ እንደሚያስፈልግ ይገልጻል[48]::

የዩኒፊኬሽን ቤተ ክርስቲያን መሥራች የሆነው ሙን፣ «ሙሴ በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን እውነት የገለጠበት፣ በአዲስ ኪዳን ዘመን ኢየሱስ የእግዚአብሔርን እውነት የገለጠበትና ሁለቱ ኪዳናት የሚቋ ጩበት (የሚደመደሙበት) የሙን ዘመን»[49] በሚል የሰብአውያን ታሪክ በሦስት ትልልቅ ክፍሎች እንደሚከፈል ያስተምራል:: ሙን «መለኮታዊ ሕግጋት» በሚል ርእስ የጻፈው መጽሐፍ፣ «በዘመኑ መጨረሻ ላይ እግዚአብሔር የዓለማትንና የሕይወትን መሠረታዊ ጥያቄ ለመመለስ መልእክተኛውን ላከ:: ስሙም ሰን ሙዮንግ ሙን ይባላል»[50]

[46] Gomes ገጽ 41 ከ Abanes, ጠቅሶ እንደ ጻፈው::
[47] An thony A. Hoekema, The Four Major Cults ( Grand Rapids: Eerdmans, 1963) ገጽ 227::
[48] You Can Live Forever in Paradise on Earth ( 1982) ገጽ 191-95:: ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር (1994) ገጽ 281-283
[49] Gomes ገጽ 42::
[50] ዝኒ ከማሁ

## 14. ትክክለኛውን የቅዱሳት መጻሕፍት አፈታት መንገድ አይከተሉም

መናፍቃን ትክክለኛ ያለሆነውን አስተምህሮአቸውን የሚያጸኑት፣ ትክክለኛ ያልሆነ የቅዱሳት መጻሕፍትን አፈታት መንገድ በመከተል ነው:: አብዛኛውን ጊዜ ይህ እውን የሚሆነው፣ አንድን ክፍል ወይም ጥቅስ ከዐውደ ምንባቡ አላቀው በመተርጐም ነው:: ለሰዋሰው አወቃቀሩ፣ ለቃላት አሰካኩ፣ ለክፍሉ ታሪካዊና ባሕላዊ ዳራ፣ ለመልከዐ ምድራዊ አቀማመጡ፣ ለክፍሉ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ ወዘተ ቦታ አይሰጡም:: በአጠቃላይ ለቋንቋ ሕግጋት ግድ የላቸውም[51]:: መናፍቃን፣ መናፍቃን የሆኑበት ዋነኛው ምክንያት ይኸው ነው:: እንቀበለዋለን የሚሉትን ዘዴ እንኳን ወጥነት ባለው ሁኔታ አይጠቀሙበትም:: በዚህ መጽሐፍ ልንዳስሳቸው ያሰብናቸውን መናፍቃን ሁሉ የሚከተሉትን የአፈታት ዘዴ በዋቢነት ማቅረብ እንችላለን፤ ነገር ግን ትምህርታቸውን በቃለ እግዚአብሔር ላይ ለማሳረፍ የተጠቀሙባቸውን አብዛኞቹን ጥቅሶች ወይም ክፍሎች ወደ ማየቱ እየዘለቅን ስለሆነ፣ ከቦታው ስንደርስ እዚያው በስፋት እንነጋገርባቸዋለን::

## 15. ቅይጥነት

ቅይጥነት የሚለውን ቃል እየተጠቀምንበት ያለነው፣ ሁለት የተለያዩ፣ አብዛኛውን ጊዜ ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን አብሮ መቀየጥ ወይም መደባለቅ የሚለውን ትርጉም እንዲወክልልን ነው:: አብዛኞቹ መናፍቃን የቅይጣዊነት ችግር አይታይባቸውም፤ ነገር ግን ከሩቅ

[51] የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥባብን በተመለከተ አያሌ መጻሕፍት የተጻፈ ቢሆንም የሚከተሉትን መጻሕፍ ማንበብ ጠቀሜታው ታላቅ ነው: Gordon D. Fee and Douglas Stuart, How to Read the Bible for All Its Worth, zd. ed ( Grand Rapids: Zondervan, 1993) ለትምህርት መለኮት ተማሪዎች Grant R. sbome, The Hermeneutical Spiral: A Comprehensive Introduction to Biblical Interpretation ( Downers Grove, Ill. : Intervarsity Press, 1991).



ምሥራቅ ትምህርት አስተሳሰብ ( ከኮንፊሽስና ከቡድሃ እምነት) ጋር የተዳበሉ ትምህርቶች ውስጥ በስፋት ይስተዋላል::

### አስረጅ

እንደ ክርስቲያን ሳይንስ፣ የእምነት እንቅስቃሴና የዮኒፊኬሽን ቤተ ክርስቲያን የቅይጥነት ችግር በስፋት ይታይባቸዋል:: እንደነዚህ መናፍቃን ትምህርት ሰማያዊ የሆነው የእግዚአብሔር ዕውቀት በስሜት ሕዋሳቶ ቻችንና በአእምሮአችን ልንደርስበት አንችልም፤ እንዲያውም በዚህ መልክ የምናውቀውን እውነት ካልኰነንን (ካልካድን) በቀር ወደ ሰማያዊው ዕውቀት ደጅ መድረስ (ማግኘት) አንችልም ይላሉ:: እንደነዚህ መናፍቃን ትምህርት መንፈሳዊውን እውነት የምንገበየው በመገለጥ ዕውቀት ብቻ ነው::

## 16. ከመናፍስቱ ዓለም ጋር መገናኘት ወይም ጥንቈላ

አብዛኞቹ መናፍቃን ከመናፍስት ዓለም ጋር የመገናኘት ችሎታ እንዳላቸው ይናገራሉ::

### አስረጅ

ለምሳሌ «የእግዚአብሔር ልጆች» የሚባለውን መናፍቃዊ ድርጅት ይመራ የነበረው ሞስስ ዴቪድ፣ ዛሬ በሕይወተ ሥጋ ከሌሉት እንደ ማርቲን ሉተር ካሉ ሰዎች ጋር ይነጋገር እንደ ነበር ገልጿል[52]::

የዩኒፊኬሽን ቤተ ክርስቲያን መሥራች የሆነው ሙን፣ « ዛሬ በዓለማችን ላይ በርካታ ሰዎች ከመንፈሳዊው ዓለም ጋር መገናኘት ችለዋል»፤ ይህም የሐሥ 2÷17 ፍጻሜ ነው[53]:: ሙንም ሆነ ባለቤቱ

[52] Gomes ገጽ44 ከ Allan, Shopping for a God, ገጽ 149 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::
[53] ዝኒ ከማሁ ገጽ 44 ከMoon, Divine Principle ገጽ 177 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

እንዲሁም ተከታዮቹ በጸሎት ጊዜ ከመንፈሳዊው ዓለም ጋር መገናኘት ይችሉ እንደ ነበር ይገልጻሉ[54]::

የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን መሥራች የነበረው ጆሴፍ ስሚዝ፣ ጠጠር እንደ መጣል ዐይነቱን ጥንቈላ ያደርግ እንደ ነበር፣ ብዙ መጻሕፍት ያስረዳሉ[55]::

## *17.መናፍቃዊ እንቅስቃሴአቸውን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ አስቀድሞ እንደ ተነበየላቸው ይገልጻሉ*

አንዳንድ መናፍቃን እነርሱ ከመምጣታቸው በፊት መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እነርሱ መምጣት አስቀድሞ የምሥራች እንደ ነገረላቸው ይገልጻሉ:: ይህ የቅዱሳት መጻሕፍትን የአፈታት መርሐ የሚቃረን ድርጊት ነው::

### *አስረጅ*

የይሖዋ ምስክሮች በሉቃስ 12÷42 ላይ «ልባምና ታማኝ ባሪያ» የተባለው ቃል የድርጅታችንን የአመራር አካላት የሚያሳይ ትንቢት ነው ባዮች ናቸው::

«የእግዚአብሔር ልጆች» በመባል የሚታወቀው መናፍቃዊ እንቅስቃሴ አባላት፣ «የእግዚአብሔር ልጆች» (1ዮሐ 3÷10፤ 5÷2) በቀጥታ ስለ እነርሱ ድርጅት እንደ ተናገረ ይገልጻሉ[56]::

[54] MC Dowe and Stewart, The Deceiver , ገጽ 177 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::
[55] ለምሳሌ:- Kurt Ven Gorden, Mormonoism. D. Michael Quinn's Early mormonism and the Magic World View ( Salt Lake City: Signature Books (1987).
[56] Gomes ገጽ 45::



ዮሴፍ ስሚዝ በዘፍጥረት ምዕራፍ 50 ላይ 14 ቊጥሮችን በመጨመር ስለ እርሱና ስለ ድርጅቱ ( የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን) የሚናገር ትንቢት እንደሆነ ይገልጻል[57]::

«የዳዊት ሥር» ለሚባለው መናፍቃዊ እንቅስቃሴ መሥራች ዴቪድ ኮርሽ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረው ንጉሥ ዳዊት ተምሳሌት (antitype) እንደ ነበር ገልጸአል[58]:: ይህ ብቻ አይደለም ኮሬሽ በኢሳይያስ 45 ላይ የተጠቀሰው የንጉሥ ቂሮስ ተምሳሌት እንደ ሆነም ያስተምር ነበር ( በዕብራይስጥ «ቂሮስ» ማለት ኮሬሽ ማለት ነው) :: ስለዚህ ዴቪድ ኮሬሽ የሚያደርገው ነገር ሁሉ እንደ ኢሳ 45÷13 መሠረት በእግዚአብሔር ምሪት ነው[59]:: ኮሬሽ በራእይ 6 ላይ የተጠቀሰው በግ እርሱ እንደሆነም ገልጸአል[60]::

## *18. ለደቃቅ አስተምህሮዎች ከፍተኛ ትኲረት ይሰጣሉ::*

ብዙ መናፍቃን ዐበይት ከሆኑት የክርስትና ትምህርቶች ይልቅ ለጥቃቅን አስተምህሮዎች ከፍተኛ ትኲረት ይሰጣሉ:: ለምሳሌ ለአለባበስ፣ ለአምልኮ ቀናት፣ ለክብረ በዓላት፣ ለባንዲራ ሰላምታ ስለመስጠት፣ ስለ ልደት ቀናት ወዘተ::

### *አስረጅ*

የይሖዋ ምስክሮች ባንዲራን ስለ መሳምና በዓላትን ስለ ማክበር ከፍተኛ ትኲረት ይሰጣሉ::

[57] ዝኒ ከማሁ ::
[58] ዝኒ ከማሁ::
[59] ዝኒ ከማሁ:: ከ Abanes, " The Branch Davidians" ገጽ 4 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::
[60] ዝኒ ከማሁ::

# ክፍል አራት
# የመናፍቃን ዕድገት ምን ይመስላል?

## ሀ. የመናፍቃን ስታቲስቲክስ በዓለማችን ላይ ምን ያህል መናፍቃን አሉ?

በዓለማችን ላይ ምን ያህል መናፍቃን አሉ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ አዳጋች የሚያደርጉት በርካታ ምክንያቶች አሉ:: ዋና ዋና ምክንያቶቹ ግን፣ ምሁራኑ ኑፋቄ ለሚለው ቃል የሚሰጡት ትንታኔ መለያየት የቁጥር ልዩነት አስከትሎአል:: ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ብዙ መናፍቃን የተከታዮቻቸውን ቁጥር በትክክል አለማወ ቃቸው ነው፤ ቢሆንም ብዙ ምሁራን፣ በዓለማችን ከ60 ሚሊዮን በላይ መናፍቃን እንዳሉ ይስማማሉ:: በዚህ ርእስ ጉዳይ ሥር በስፋት ለመመልከት የምንሞክረው በተለያዩ አጋጣሚዎች ይፋ የሆኑትን የአገራችንን ዐበይት መናፍቃን ስታቲስቲክስ ነው::

## ለ. የይሖዋ ምስክሮች ዓለም ዐቀፋዊ ስታቲስቲክስ[1]

### 1. የአባላት ብዛት

እንደ ጐርጐሮሳውያን የዘመን አቈጣጠር በ1997ዓ.ም. ላይ በ232 አገሮች በተደረገው ቈጠራ፣ ንቁ የይሖዋ ምስክር ተሳታፊ

[1] ይህ መረጃ በብዛት የተወሰደው ተስፋዬ ሮበሌ የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን (ራእይ አሳታሚ ድርጅት፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ 1991ዓ.ም) ገጽ 16-24 ላይ ነው::

አባላት ቍጥር 5,599,931 ሲሆን፣ ይህ ቍጥር በ1998 ዓ.ም. ወደ 6 ሚሊዮን አሻቅቦአል:: በ1997 ዓ.ም. ላይ በተደረገው የ«መታሰቢያ» አገልግሎት [የይሖዋ ምስክሮች የጌታን ራት የሚያስቡበትን ቀን «የመታሰቢያ አገልግሎት» (Memorial Service) ብለው ይጠሩታል] 14,322,226 ሰዎች ፕሮግራሙን ተካፍለዋል[2]:: ይህ ቍጥር የሚያመለክተን የይሖዋ ምስክሮች ከንቍ ተሳታፊ አባሎቻቸው ዕጥፍ በላይ በሆኑ ሰዎች ላይ አዎንታዊ ተጋቦት እንዳላቸው ነው::

በዓለም ዙሪያ በአንድ ደቂቃ ከ45 ሴኮንድ ውስጥ አንድ ሰው የይሖዋ ምስክር አባል ይሆናል[3]:: በዓለማችን 73,070 የይሖዋ ምስክር ጉባኤዎች[4] ይገኛሉ::

## *2. የዕድገት መጠን*

የይሖዋ ምስክሮች የዕድገት ፍጥነት እጅግ አስደንጋጭ ነው:: በ1965 ዓ.ም. 1.1 ሚሊዮን የነበረው የንቁ ተሳታፊ አባላት ቍጥር በ1980 ዓ.ም. ወደ 2.2 ሚሊዮን፣ በ1992 ዓ.ም. ደግሞ ወደ 4.4 ሚሊዮን ዕድገት አሳይቶአል:: በ1994 ዓ.ም ላይ በሶቭየት ኅብረት ብቻ 27,000 ሰዎችን አጥምቀዋል[5]:: በየዓመቱ በዓለም ላይ 50 አዳዲስ ጉባኤዎች ይቋቋማሉ[6]::

[2] " 1998 Year book of Jehovah's Witness" ገጽ 31
[3] ዝኒ ከማሁ::
[4] የይሖዋ ምስክሮች ስብሰባቸውን «ጉባኤ» ብለው ይጠሩታል::
[5] Christian Research Institute, " Cult Growth Statistics" ከ «መጠበቂያ ግንብ» (ጥር 1 ቀን 1993) ገጽ 15:26 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::
[6] ዝኒ ከማሁ:: የመጠበቂያ ግንብ ቪዲዮ: Jehovah's Witnesses:the **Organization Behind the Name** (1990) ላይ ጠቅሶ እንደ ጻፈው::



## *3. ሚስዮናዊ እንቅስቃሴ*

የይሖዋ ምስክሮች በ1997 ዓ.ም ብቻ ለመስክ ምስክርነት 1,179,735,841 ሰዓት አውለዋል[7]:: ይህን ቍጥር ለንቁ ተሳታፊ አባሎች ቍጥር ስናካፍለው እያንዳንዱ አባል ለመስክ ምስክርነት፣ በዓመት ከ200 ሰዓት በላይ ተጠቅሞአል ማለት ነው:: በ1997 ዓ.ም ላይ የተከታዮቻቸውን ልጆች ቍጥር ጨምሮ 375,923 ሰዎች አጥምቀዋል[8]:: ይህ የሚያሳየን የይሖዋ ምስክሮች ለአንድ ሰው በአማካኝ 3,500 ሰዓት መጠቀማቸውን ነው[9]:: አንድ ንቍ የይሖዋ ምስክር ተሳታፊ አባል፣ በአማካኝ በአንድ ወር 18 ሰዓትን ለመስክ ምስክርነት ያውላል[10]:: በ1970 ዓ.ም አንድ ንቍ አባል በዓመት «ለመስክ አገልግሎት»[11] 150 ሰዓትን ያውል የነበረ ሲሆን፣ በ1992 ዓ.ም ይህን ሰዓት በማሻሻል አንድ አባል በዓመት 236 ሰዓት በመስክ ምስክርነት ላይ ያሳልፋል[12]::

## *4. የጽሑፍ ሥርጭትና የመገናኛ ብዙኃን*

ከማንኛውም መናፍቃን ይልቅ፣ የጽሑፍ ውጤቶች በከፍተኛ ደረጃ እየተጠቀሙ ያሉት፣ የይሖዋ ምስክሮች ናቸው:: የመጠበቂያ ግንብ በዓለም ዙሪያ 33 ታላላቅ ማተሚያ ቤቶች አሉት:: «ቤቴል» በመባል የሚታወቀው ትልቁ የድርጅቱ ማተሚያ ቤት፣ በቀን ርዝመቱ 1000 ማይል (1609 ኪሎ ሜትር) ወረቀት ወይም 61 ሚሊዮን ገጽ ያትማል[13]:: ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በወር 3 ሚሊዮን የአዲሲቱን

[7] « 1998 Yearbook of Jehovah's Witnesses" ገጽ 31::
[8] ዝኒ ከማሁ ገጽ 31 ::
[9] Robert M. Bowman, Jr. Jehovah's Witnesses ( Grand Rapids Zon, 1995) ገጽ 14::
[10] ዝኒ ከማሁ ገጽ 15 ::
[11] « የመስክ አገልግሎት» የሚባለው በየመንገድ ዳሩና በየቤቱ የመጠበቂያ ግንብ ወንጌልንና ጽሑፎች ማሠራጨት ነው::
[12] Robert M. Bowman, Jr. Jehovah's Witnesses ገጽ 16::
[13] CRI "Cult Growth Statistics" የመጠበቂያ ግንብ ( ጥር 1 ቀን 1993 ) ገጽ 19 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

ዓለም ትርጒም[14] እያተመ ያወጣል:: በ1991 ዓ.ም በእነዚህ 33 ማተሚያ ቤቶች የሚሠሩ 11,000 የሙሉ ጊዜ ሠራተኞች ነበሩ[15]::

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ጽሑፎቹን በ210 ቋንቋዎች ያስተረጒማል:: «መጠበቂያ ግንብ» በሚል ርእስ የሚታወቀው መጽሔት በብዛት ከሚታተሙት መጽሔቶች ውስጥ ዋነኛው ነው:: መጽሔቱ በወር ሁለት ጊዜ የሚታተም ሲሆን፣ በእያንዳንዱ እትም ከ16 ሚሊዮን በላይ ቅጆች ይባዛሉ፤ ከ120 በሚበልጡ ቋንቋዎችም ይተረጐማሉ:: ከዐሥራ አምስት ሚሊዮን የሚበልጠው ቅጅ የሚታተመው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ነው:: ሥርጭቱም ሪደርስ ዳጀስትና ቲቪ ጋይድ የሚባሉት መጽሔቶች ካላቸው ሥርጭት ጋር የሚስተካከል፣ ሸያጩም ታይምስ፣ ኒውስዊክ፣ ዩኤስ ኒውስና ወርልድ ሪፓርት ከሚባሉት የዓለማችን ዕውቅ መጽሔቶች ጋር ይወዳደራል[16]::

- «ንቁ» በመባል የሚታወቀው የድርጅቱ መጽሔት በ13 ሚሊዮን ቅጆች ሲባዛ በ75 ቋንቋዎች ይተረጐማል[17]::

የአዲሲቱ ዓለም ትርጒም በ1990 ዓ.ም ብቻ በ67 ሚሊዮን ቅጆች የተባዛ ሲሆን በ14 ቋንቋዎች ተተርጒሞ ለንባብ በቅቶአል:: በአሁኑ ጊዜ ይህ መጽሐፍ ከ16 በሚበልጡ ቋንቋዎች ተተርጒሞአል[18]::

«ወደ ዘላለም ሕይወት የሚመራው እውነት» በሚለው ስያሜ ተጽፎ የታተመው መጽሐፍ በ1968 ዓ.ም ላይ ለንባብ የበቃ ሲሆን፣

[14] «የአዲሲቱ ዓለም ትርጒም» የሚባለው የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር ከግሪክና ከዕብራይስጥ ወደ እንግሊዝኛ ተርጒሜዋለው የሚለው ቅጅ ነው:: መጽሐፉ ከድርጅቱ አስተምህሮ ጋር እንዲጣጣም ተደርጉ የተተረጐመ በመሆኑ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ፣ የዕብራይስጥና የግሪክ ሊቃውንት ከፉኛ የኰነኑት መጽሐፍ ነው::

[15] David A. Reed, Jehovah's Witness Literature: a Critical Guide to Watchtower Publications ( Grand Rapids Baker, 1993) ገጽ 9::

[16] Alan W. Gomes, Unmasking the Cults ገጽ 23::

[17] Robert M. Bowman, Jr. Jehovah's Witnesses ገጽ 15

[18] Alan W. Gomes, Unmasking the Cults ገጽ 23



በሥርጭት ደረጃ ቀዳሚውን ስፍራ ከያዙት አምስት መጻሕፍት መካከል አንዱ ሊሆን በቅቶአል[19]::

# ሐ. የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክስ በኢትዮጵያ

እንደ ጐርጐሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ1991ዓ.ም በኢትዮጵያ 3,020 የነበረው የይሖዋ ምስክሮች ቍጥር፣ በ1997 ዓ.ም ላይ ወደ 5,649 አሻቅቦአል[20]:: በ1991 ዓ.ም ለመስክ ምስክ(ር)ነት ይወጡ የነበሩት የይሖዋ ምስክሮች 2,730 ሲሆኑ በ1997 ዓ.ም ወደ 5,292 ከፍ ብሎአል:: ከ1991 ዓ.ም እስከ 1997 ዓ.ም ድረስ የታየው ዓመታዊ የዕድገት መጠን በአማካኝ 15 በመቶ ነው:: ይህ ማለት ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ በሉት ሰባት ተከታታይ ዓመታት 4,158 ሰዎችን አጥምቀዋል:: ድርጅቱ በ1991ዓ.ም 483 አቅኚዎች[21] የነበሩት ሲሆን፣ ይህ ቍጥር በ1997 ዓ.ም ወደ 916 አሻቅቦ ይገኛል:: በ1991 ዓ.ም በአገሪቱ ዙሪያ 54 ጉባኤዎች የነበሩ ሲሆን፣ በ1997 ዓ.ም ወደ 79 ዐድጓአል:: በ1997 ዓ.ም ለመስክ አገልግሎት የዋለው ሰዓት 1,570,141 ሲሆን፣ ይህን ቍጥር ለንቁተሳታፊ አባላት ቍጥር ስናካፍለው እያንዳንዱ የይሖዋ ምስክር በአንድ ዓመት ብቻ 278 ሰዓት ለመስክ ምስክርነት አውሎአል:: በ1997 ዓ.ም ላይ በመዲናችን መኻል በሚገኘው የእግር ኳስ መጫወቻ ሜዳ (ስቴዲዮም) ባደረጉት የመታሰቢያ ቀን 15,716 ሰዎች ፕሮግራሙን መካፈላቸው፣ ከአባሎቻቸው ዕጥፍ የሚሆኑ ሰዎች ልባቸውን ለይሖዋ ምስክሮች በመክፈት ፕሮግራማቸውን እንደሚካፈሉ የሚያመለክት ነው::

[19] Bowman ገጽ 15

[20] በግርጌ ማስታወሻ ካልተመለከተ በስተቀር መረጃዎቹ ሁሉ የተገኙት "Year book of Jehovah's Witnesses" በሚል ስያሜ ድርጅቱ በየዓመቱ ከሚያወጣቸው መጻሕፍት ላይ ነው::

[21] የድርጅቱ የሙሉ ጊዜ ሠራተኞች አቅኞች ይባላሉ::

# *መ. የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ስታቲስቲክስ በኢትዮጵያ* [1]

## *1. የአባላት ብዛት*

በ1961ዓ.ም[2] ከአሜሪካን አገር በመጡ የድርጅቱ ሚስዮናውያንና በተክለማርያም ገዛኸኝ የተጀመረው እንቅስቃሴ[3]፣ ዛሬ 1.6 ሚሊዮን አባል፣ ከ4 ሺህ በላይ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት[4]፣ ከ4 ሺህ በላይ አገልጋዮች እንዳሉት ይገልጻል:: ይህ ማለት በየዓመቱ ከ46 ሺህ ያላነሱ ሰዎች የድርጅቱን እምነት በመቀበል የቤተ ክርስቲያኒቱ ሙሉ አባል የሚሆኑ ሲሆን፣ በየዓመቱ የሚመጡትንም ተጨማሪ አባላት ለማስተናገድ ከ 11 በላይ የሆኑ ቤተ ክርስቲያናት ይቈረቈራሉ[5]::

በአዲስ አበባ፣ ልዩ ስሙ ጎፋ መብራት ኀይል በሚባለው አካባቢ የታነጸው የማምለኪያና የማስተማሪያ ሕንፃ፣ በአባላት ብዛት ብቻ ሳይሆን በገንዘብ ዐቅማቸውም ጠንካራ መሆናቸውን የሚያመላክት ነው[6]::

## *2. የዕድገት መጠን*

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ያለው ዕድገት እጅግ አሳሳቢ ነው:: በ1961ዓ.ም በሁለት አሜሪካውያንና በአንድ ኢትዮጵያዊ

---

[1] ይህ ስታቲስቲክሳዊ መረጃ በአብዛኛው የተወሰደው ሚያዝያ 24 ቀን 1993 ዓ.ም ከተክለማርያም ገዛኸኝ ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ነው::

[2] በዚህ ርእስ ሥር የሚገኘው የዘመን አቈጣጠር እንደ ኢትዮጵያውያን የዘመን አቈጣጠር ነው::

[3] ተክለማርያም ገዛኸኝ እንቅስቃሴውን የጀመርኩት ጌታ ራሱ በ1958 ዓ.ም ትምህርቱን ከገለጠልኝ በኋላ ነው ቢልም፣ ትምህርቱን ያገኘውና የተጠመቀው በሚስዮናውያኑ ነበር:: እነዚህ ሚስዮናውያን ( ቴኔዝ ዊድልና ባለቤታቸው ) ከዩናይትድ ፔንቲኮስታል ቤተ ክርስቲያን የመጡ ናቸው::

[4] እንደ ተክለማርያም ገዛኸኝ ይህ ቍጥር ድርጅቱ፣ « Preaching point » የሚለውና ከ6-10 ሰዎችን የያዘ የአምልኮ ማእከላትን የሚያካትት ነው::

[5] ይህ ቍጥር የተጋነነ ለመሆኑ በርካታ ማስረጃዎች አሉ::

[6] አንዳንድ ምንጮች ድርጅቱ አሜሪካን አገር ከሚገኙ መሰል ድርጅቶች፣ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ እርዳታ እንደሚያገኝ ይገልጻሉ:: ድርጅቱ በኬኒያ፣ በደቡብ አፍሪካና በአሜሪካ እንዲማሩለት የላካቸውን አገልጋዮች የሚያሠለጥነው በውጪ እርዳታ እንደሆነ ምንጮቹ ያስረዳሉ::

# ሠ. የሞርሞኖች ዓለም ዐቀፋዊ ስታቲስተክስ

## 1. የአባላት ብዛት

እንደ 1991ዓ.ም ዘገባ 8,120,000 ሞርሞኖች በዓለማችን ይኖራሉ[1]:: በ1995 ዓ.ም ላይ ወደ 9,000,000 እንደ ነበሩ አንዳንድ መረጃዎች ያመለክታሉ[2]:: ሞርሞኖች በ146 አገሮች 20,000 ቤተ አምልኮዎች አሉአቸው[3]:: በ1992 ዓ.ም 77,380 ሕፃናትን አጥም ቀዋል[4]:: በ1992 ዓ.ም ብቻ 274, 477 ሰዎች የሞርሞንን እምነት ተቀብለዋል (በ1990 ዓ.ም እምነቱን የተቀበሉ ሰዎች 330,877 ነበሩ)[5]::

## 2. የዕድገት መጠን

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀምሮ በየ15 ዓመቱ ቁጥራቸው በዕጥፍ ሲያድግ፣ ከ1970 እስከ 1985 ዓ.ም ባሉት ዓመታት ግን ይህ ቁጥር በሦስት ዕጥፍ ጨምሮአል[6]:: በዓለማችን በ1.55 ሰኮንድ ውስጥ፣ አንድ ሰው የሞርሞንን እምነት ይቀበላል[7]:: ከዚህ ቁጥር ውስጥ ሦስት አራተኛውን ወይም 75 በመቶ የሚሆኑት ቀድሞ የወንጌላውያን ቤተ ክርስትያናት (ፕሮቴስታንት) አባል የነበሩ ሰዎች ናቸው[8]:: ሞርሞኖች

---

[1] Gomes ገጽ 19 ከChurch News ( ሚያዝያ 11 ቀን 1992) ገጽ 4 ላይ ጠቅሶ እንደ ጻፈው::
[2] Gomes ገጽ 20
[3] CRI " Cult Growth Statistics" (መስከረም 1993) ከ The Endsign? (ግንቦት 1993) ገጽ 22 ላይ ጠቅሶ እንደ ጻፈው::
[4] Gomes ገጽ 20
[5] Church News (ሚያዝያ 10 ቀን 1993) ገጽ 23
[6] Gomes ገጽ 20 ላይ ከJohn Heinerman and Anson Shupe, The Mormon Corporate Empire (Boston:Beacon Press, 1985) ገጽ 81 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::
[7] CRI, " Cult Grcwth Statistics" ከThe En sign? ( ግንቦት 1993) ቍ22 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::
[8] Josh Mc Dowell&Don Stewart, The Deceivers what Cults Believe, How They Lure Followers (San Bernarding, Calif:Here's Life Pub. 1992)ገጽ 16

እጅግ ስኬታማ የሆኑት በአሜሪካን አገር ነው:: በአሁኑ ወቅት ቊጥራቸው ከ14 ሚሊዮን በላይ እንደሆነ ይገመታል[9]::

## 3 ሚስዮናዊ እንቅስቃሴ

የሞርሞን ወጣቶች የራሳቸውን ወጪ በመሸፈን በሚሲዮናዊነት ለሁለት ዓመት እንዲያገለግሉ ድርጅቱ ያበረታታል[10]:: ለድርጅቱ በሚስዮናዊነት ለሁለት ዓመት የሚያገለግሉ ወጣቶች ከ46,000 በላይ ሲሆኑ፣ ለሚስዮናዊ አገልግሎታቸውም በየዓመቱ 1.5 ቢሊዮን ዶላር ወጪ ይደረጋል[11]::

## 4. የጽሑፍ ሥርጭትና የመገናኛ ብዙኃን

ሞርሞኖች በ1990 ዓ.ም በአሜሪካንና በካናዳ ባደረጉት ድርጅቱን የማስተዋወቅ ሥራ 679,815 ሰዎች ምላሽ ሲሰጡ፣ 198,091 ሰዎች የሞርሞን ሚስዮናውያን ቤታቸው ድረስ በመምጣት እንዲያ ነጋግሩአቸው ጋብዘዋል[12]:: የሞርሞን መጽሐፍ (Book of Mormon) የተባለውን መጽሐፍ በነጻ ያሠራጫሉ:: ይህ መጽሐፍ ለድርጅቱ ዕድገት ታላቅ አስተዋፅኦ ያመጣ ሲሆን[13]፣ በ79 ቋንቋዎችም ተተርጒሞ በነጻ በመሠራጨት ላይ ነው[14]:: አባላቱ በ1990ዓ.ም እንደ ድርጅቱ አስተምህሮ ከመጽሐፍ ቅዱስ እኩል የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል ነው የሚሉትን፣ «መጽሐፈ ሞርሞን» በ3.27 ሚሊዮን ቅጅ አሠራጭተዋል::

---

[9] Gomes ገጽ 20 Heinerman&Shupe, The Mormon Corporate Empire, ገጽ 81 ላይ ጠቅሶ እንደ ጻፈው::
[10] አብዛኛውን ወጪ የሚሸፍኑት የወጣቶቹ ወላጆች ናቸው:: ይህም ወጪ ወላጆች ለድርጅቱ ከሚከፍሉት የወር ዐሥራት በተጨማሪ ነው::
[11] CRI, " Cult Growth Statistics."ከ The Ensign ( ግንቦት, 1993) ገጽ 22 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::
[12] Gomes ገጽ 21
[13] Gomes ገጽ 21Dockstader " Media Powerful Tool in Conversions." ገጽ 7 ላይ ጠቅሶ እንደ ጻፈው::
[14] ዘኒ ከግሁ ከ The Ensign (ሚያዝያ 1991) ገጽ 75 ጠቅሶ እንደ ጻፈው:: በ1993 ዓ.ም የሞርሞን መጽሐፍ በአማርኛ ተተርጒሞአል::



## 5. የገንዘብ ዐቅም

የድርጅቱ የገንዘብ ዐቅም ለመጀመሪያ ጊዜ ይፋ የሆነው በ1959 ዓ.ም ነው:: ድርጅቱ በዓመት 4.7 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ያለው ሲሆን፣ ከንግድ ደግሞ በዓመት 3 ቢሊዮን ዶላር ያገኛል:: አጠቃላይ ድምሩን ስናሰላው በሀብት በልጽገዋል ከሚባሉት የዓለማችን አብዛኞቹ አገሮች ከሚያገኙት ዓመታዊ ገቢ በዕጥፍ የሚበልጥ ነው[15]:: ለድርጅቱ የገንዘብ ዐቅም ዋነኛ ምንጭ የአባላቱ ዐሥራት ሲሆን፣ ከዚህም በቀን 3 ሚሊዮን ዶላር ይሰበሰባል[16]:: ከሮማዋ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ቀጥሎ በገንዘብ ሀብታሙ፣ የሞርሞኖች ድርጅት ነው[17]::

---

[15] CRI, "Gult Growth Statistics. ከ Arizona Republic (ከሰኔ 30-ሐምሌ 3 ቀን 1991) ጠቅሶ እንደ ጻፈው::
[16] Gomes ገጽ 21 Kurt Van Gorden's Mormonism ጠቅሶ እንደ ጻፈው::
[17] Kurt Van Gorden's Mormonism.

# ረ. የባሃኢ እምነት ስታቲስቲክስ በኢትዮጵያ

## 1. የአባላት ብዛት

በአዲስ አበባ የሚገኘው የባሃኢ ማእከል ባወጣው ዘገባ መሠረት፣ በዓለማችን በሚገኙ 300 የሚደርሱ አገሮችና ጥገኛ ግዛቶች ውስጥ 2,100 ጐሣዎች ውስጥ የእምነቱ ተከታዮች አሉ:: በእነዚህም አገሮች ውስጥ 20,000 የሚደርሱ ቤተ አምልኮዎች አሏቸው:: በ1992 ዓ.ም የወጣው ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ፣ «ከክርስትና ቀጥሎ በዓለማችን ላይ በከፍተኛ ሁኔታ የተሠራጨ ሃይማኖት» መሆኑን ይጠቁማል[9]::

አርኖልድ ቶይንቢ የተባሉት የታሪክ ምሁር፣ «የባሃኢ እምነት ምናልባት የወደፊቱ የዓለማችን ሃይማኖት ሊሆን ይችላል»[10] የሚል አስተያየት ሰንዝረዋል:: በአሁኑ ወቅት የባሃኢ እምነት ትልቅ ተቀባይነት በማግኘት ላይ ያለ ሃይማኖት ነው:: በአሜሪካን አገር ብቻ ከ1963 ዓ.ም ጀምሮ በየዐሥር ዓመት ውስጥ በዕጥፍ እያደገ ነው:: በ1982 ዓ.ም በተደረገው ቈጠራ መሠረት በአሜሪካን አገር ብቻ 110,000 አባላት ነበሩት[11]:: በአሜሪካን አገር የባሃኢን እምነት በመቀበል ላይ ያሉት ከ15 እስከ ሠላሳ ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉና ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ወጣቶች ናቸው[12]:: በ1982 ዓ.ም ዘገባ መሠረት በዓለማችን ከ5 ሚሊዮን የሚበልጡ የባሃኢ እምነት ተከታዮች አሉ:: በዓለማችን ከፍተኛ የሆነው የባሃኢ እምነት ተከታዮች የሚገኙት በሕንድ አገር ሲሆን፣ በ1982 ዓ.ም ዘገባ መሠረት ቍጥራቸው ከ 1.5 ሚሊዮን በላይ ሆኖአል[13]::

---

9 The Baha'i Faith in Ethiopia (የባሃኢ ማእከል ያወጣው ያልታተመ ጽሑፍ) ገጽ 1::
10 Edmond C.Gruss. Cults and the Occult .(Phillipsburg Jersey: Pres. and Reformed Pub.1982)ገጽ 146::
11 ዝኒ ከማሁ::
12 ዝኒ ከማሁ::
13 ዝኒ ከማሁ::

መነሻውን ከአዲስ አበባ ያደረገው የባሃኢ እምነት በጂማ፣ በደብረ ዘይት፣ በናዝሬት፣ በአንቦ፣ በሰበታ፣ በሆለታ፣ በወሊሶ፣ በአዋሳ ወዘተ ተሠራጭቶአል[14]:: በ1973 ዓ.ም በሲዳሞ ብቻ 56 ሰዎች እምነቱን መቀበላቸው ተዘግቦአል[15]:: ይህ ቊጥር በ1970ዎቹ መጨረሻ ላይ ወደ 264 አሻቅቦአል[16]:: በአሁኑ ወቅት የባሃኢ እምነት 51«አጥቢያ ቤተ አምልኮዎች» አሉት[17]::

### 2. ሚስዮናዊ እንቅስቃሴ

ለባሃኢ እምነት መስፋፋት ትልቅ ሚና የሚጫወቱት[18]:-

- እምነቱ ለሰው ልጆች አለኝ የሚለው ፓለቲካዊና ማኅበራዊ ችግሮችን የመፍታት ዕቅድ::
- ለግብረገባዊ ግንኙነቶች አለኝ የሚለው ታላቅ መስፈርት::
- እያንዳንዱ አባል በድርጅቱ ሥራ ውስጥ ተካፋይ መሆኑ፤ እንዲሁም
- ለሚስዮናዊነት የሚሰጡት ትልቅ ስፍራ በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው::

«ፓዮኔር» ወይም «አቅኚ» በመባል የሚታወቁት የድርጅቱ ሚስዮናውያን እምነቱን ለማስፋፋት አገራቸውን ትተው፣ አገር አቋርጠው ይሄዳሉ:: ለዚህም ነው እምነቱ፣ «ከክርስትና ቀጥሎ በከፍተኛ ፍጥነት በመስፋፋት ላይ ያለ ሃይማኖት» የተባለው[19]::

---

[14] The Baha'i Faith in Ethiopia ገጽ 4
[15] ዝኒ ከማሁ::
[16] ዝኒ ከማሁ::
[17] ዝኒ ከማሁ::
[18] Edmond C.Gruss. ገጽ 151::
[19] ዝኒ ከማሁ ከ Kezmoh, "Working for the Unity of Mankind"ገጽ 22 ጠቅሶ እንዳ ስፈረው::



# ክፍል አምስት
# መናፍቃን የመበራከታቸው ምስጢር ምንድን ነው?

## ሀ. ሰዎች መናፍቃንን ለምን ይከተላሉ?[1] አጠቃላይ አሰሳ

### 1. የግል ፍላጎት ምክንያት ሊሆን ይችላል

አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች የራሳቸው የሆኑ የተለያዩ ችግሮች አሉባቸው፤ መናፍቃን ደግሞ ይህን ችግር እንደሚፈቱላቸው ቃል ይገቡላቸዋል:: እንዲያውም ለችግሮቹ አማራጭ የማይገኝላቸው መፍትሔዎች በእነርሱ ዘንድ እንዳሉ ያውጃሉ::

መናፍቃን የተከታዮቻቸውን ፍላጎት ለጥቂት ጊዜ ሊያሟሉ ይችሉ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ለችግሮቹ የሚሰጡት መፍትሔ ዘላቂነትም ሆነ እውነተኛነት ሊኖረው አይችልም:: ምክንያቱም ለሰዎች ችግር ትክክለኛና ዘላለማዊ መፍትሔ ከሚሰጠው ከእውነተኛው ወንጌል ርቀዋልና:: ከዚህም የተነሣ የተከታዮቻቸውን ፍላጎት ማርካት ይሳናቸዋል:: የሰዎችን ፍላጎት ዘላቂ በሆነ መልኩ ማርካት የሚችለውና ጥያቄዎቻቸውን መመለስ የሚችለው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነውና::

---

[1] ይህ ክፍል የተወሰደው: ተስፋዬ ሮበሌ የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን (ራእይ አሳታሚ ድርጅት፤ አዲስ አበባ 1991) ገጽ 151-158 ከሚባለው መጽሐፍ ሲሆን፣ ጸሓፊው አብዛኛውን መረጃ ያገኘው Alan W. Gomes, Unmasking the Cults (Grand Rapids: Zondervan, 1995) ገጽ 81-85 ከሚባለው መጽሐፍ ነው::

ክሩት ቫን ጎርደን የሚባሉት የትምህርተ መለኮት ሊቅ «መናፍቃንን በወንጌል መድረስ» በተሰኘው መጽሐፋቸው ላይ ሰዎች መናፍቃንን በመከተል ሊያረኩት የሚሹትን የፍላጎት ዐይነት በአራት ክፍል መድበዋቸዋል። ይኸውም፡- አእምሮአዊ ፍላጎት፣ ስሜታዊ ፍላጎት፣ ማኅበራዊ ፍላጎትና መንፈሳዊ ፍላጎት ይባላሉ[2]። ማንኛውም ሰው እነዚህ ፍላጎቶች በተለያየ መጠን ስላሉት፣ ፍላጎቶቹ በራሳቸው መጥፎ አይደለም። እነዚህን ተገቢ ፍላጎቶች በእግዚአብሔር ቃል እውነት ያለማርካት፣ ሰዎች በመናፍቃዊ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዳይሳቡ ወይም አዲስ መናፍቃዊ እንቅስቃሴ እንዲጀመሩ ሊያስገድዳቸው ይችላል።

## *2. አስተምህሮ ምክንያት ሊሆን ይችላል*

ሰዎች ትክክለኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ከተረዱ በኋላ፣ የተረዱትን እውነት ትተው መናፍቃዊ እንቅስቃሴ ውስጥ አይገቡም ብሎ ማሰብ አግባብ ላይሆን ይችላል። ነገር ግን በአንጻራዊነት ሲታይ በዚህ መልኩ መናፍቃንን የሚከተሉ ሰዎች በጣም ጥቂት ናቸው። በአሜሪካን አገር በተደረገው ጥናት መሠረት፣ አብዛኞቹ ሰዎች የሞርሞንን እምነት የሚቀበሉት፣ ሞርሞኖች ምን ዐይነት እምነት እንዳላቸው አስቀድመው ካወቁ በኋላ ነው።

## *3. ቤተ ክርስቲያን ማሟላት ያለባትን ሳታሟላ ስትቀር*

ሰዎች ቤተ ክርስቲያን እንድታሟላላቸው የሚፈልጉትን ነገር ተሟልቶ ካላገኙት፣ መናፍቃዊ እንቅስቃሴ ሊጀምሩ አልያም በተጀመረው እንቅስቃሴ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። ሦስት አራተኛ የሚሆኑት

[2] ዝኒ ከማሁ Kurt Van Gorden. "Unity School of Christianity" in Evangelizing the Cults ገጽ 140 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።



የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን አባላት በአንድ ወቅት የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን አባላት የመሆናቸው[3] ጉዳይ፣ ይህንኑ እውነት የሚያጠናክር ነው።

ቫን ባለን መናፍቅነትን፣ «ያልተከፈለ የቤተ ክርስቲያን ዕዳ»[4]። ብሎ ይጠራዋል። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን መሙላት ያቃታትን ባዶነት መናፍቃን እየሞሉ ብዙዎችን በማሳሳት ላይ ስላሉ ነው። ከጊዜ ወደ ጊዜ የመናፍቃን ቊጥር እየጨመረ መምጣት፣ የቤተ ክርስቲያንን ጉድለት የሚያሳይ ነው። ይህ ሲባል ግን፣ ቤተ ክርስትያን የሰዎችን ተገቢ ፍላጎት እንደ ቃለ እግዚአብሔር ለማርካት ምንም ዐይነት ጥረት አላደረገችም ማለት አይደለም፤ ባንጻሩም ቤተ ክርስቲያን የአባሎቿን ፍላጎት ማርካት የምትችለው የምእመናኑ ፍላጎት ሲታከልበት እንደ ሆነም መዘንጋት የለብንም፤ ቢሆንም ግን ቤተ ክርስቲያን የአባሎቿን መንፈሳዊ፣ አእምሮአዊ፣ ማኅበራዊና አካላዊ ፍላጎት እንደ እግዚአ ብሔር ቃል የማርካት ታላቅ ኀላፊነት አለባት።

[3] ዝኒ ከማሁ ገጽ 152 Josh Mc Dowell and Don Stewart, Assisted by Kurt Van Gorden The Deceivers: What Cults Believe, How They Lure Followers (San Bernardino, Calif Here's Life Publishers, 1992) ገጽ 16 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[4] ዝኒ ከማሁ Van Baalen, Chaos of the Cults. ገጽ 390 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

# ለ. ሰዎች መናፍቃንን በመጠጋት ሊያሟሏቸው የሚሹአቸው ፍላጎቶች

## 1. ፍቅር

ሰዎች መናፍቃንን ከሚጠጉባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ፍቅርና ክብካቤ ፍለጋ ነው። ይህን በበቂ ሁኔታ ካገኙ ባገኙባቸው ስፍራዎች እስከ መጨረሻው ለመቆየት ይገደዳሉ። መናፍቃንን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት አዳጋች ከሚያደርጓቸው ምክን ያቶች ውስጥ ይህ አንዱ ነው። ሰዎች፣ «ዩኒቲ ስኩል ኦፍ ክርስ ቲያኒቲ» በሚባለው መናፍቃዊ ድርጅት እንዲሳቡ የሚያደርጋቸው፣ ድርጅቱ ለፍቅር ከፍተኛ ስፍራ ስለሚሰጥ ነው[5]።

## 2. ቤተ ሰብ

ወጣቶች መናፍቃንን ከሚከተሉባቸው ምክንያቶች አንዱ፣ ለጊዜውም ቢሆን የሚንከባከባቸው ቤተ ሰብ ስለሚፈልጉ ነው። የቤተ ሰብ መፍረስ፣ በወላጆችና በልጆች መካከል የማያቋርጥ ጠብ መኖር እንዲሁም አግባብ ባልሆነ መልኩ ልጆችን መቅጣት፣ ወጣቶች አዲስ ቤተ ሰብ እንዲፈልጉ ያደርጋቸዋል።

## 3. ተፈላጊነትና ክበሬታን ማግኘት

ሰዎች በኅብረተ ሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ካጡ ወይም ቤተ ሰባዊነት የማይሰማቸው ከሆነ፣ አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ ለመናፍቃን እንቅ ስቃሴ ተጋልጠዋል ማለት ነው። ምክንያቱም ተፈላጊነትን፣ ተቀባይነ

[5] ዝኒ ከማሁ ገጽ 153 Mc Dowell & Stewart, The Deceivers ገጽ 18 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

ትንና ከበሬታን እናገኝበታለን ብለው ወደሚያስቡበት ስፍራ ሁሉ ለመሄድ አያቅማሙምና:: ብዙ መናፍቃን ደግሞ ተፈላጊነትን፣ ተቀባይነትንና ከበሬታን ያለገደብ እንደሚሰጡ ያውጃሉ:: ታዲያ እነዚህን ነገሮች አጥብቆ ሲፈልጋቸው የነበረው ሰው በቀላሉ ይወሰዳል::

መናፍቃን ለተራው አባላቸው እንኳ የአገልግሎት ስፍራ ይሰጣሉ:: ይህም የእያንዳንዱን አባል አስፈላጊነት ከፍ ያደርገዋል:: ሞርሞኖች፣ «ክህነታዊ ሥራ» የሚሉትን አገልግሎት ትኩረት ይሰጡታል:: ወጣቶቻቸው የራሳቸውን ወጪ በመሸፈን የሁለት ዓመት ሚስዮናዊ አገልግሎት ያገለግላሉ:: የይሖዋ ምስክሮች አባሎቻቸውን በሙሉ በማንቀሳቀስ ቤት ለቤት በመሄድ እንዲሁም በየመንገድ ዳር የመጠበቂያ ግንብ ድርጅትን ወንጌል ይሰብካሉ፤ ጽሑፉንም ያሠራጫሉ[6]::

## 4. አካላዊ ፍላጎትን ማርካት

አንዳንድ መናፍቃን የምግባረ ሠናይን ተግባር ሲያከናውኑ ይታያሉ፤ ይኸውም የተራበን ያበላሉ፣ የታረዘን ያለብሳሉ፣ ቤተ ሰብ የሌላቸውን ልጆች በማደጎ ወስደው ያሳድጋሉ::

ለትምህርት ያላቸው ዕቅድ፣ ድርጅቶቻቸውን ለማስታወቅ የሚጠቀሙበት መንገድና ዘዴ እንዲሁም የመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀማቸው፣ ከእኛ እጅግ ብዙ ርቀው እንዲሄዱ አድርጓቸዋል::

## 5. መንፈሳዊ ፍላጎትን ማርካት

አንዳንድ ሰዎች መናፍቃንን የሚከተሉት መንፈሳዊ ረሓባቸውን ለማጥገብ ነው:: መንፈሳዊ ረሓብ በማጥገብ ረገድ፣ «የእምነት እንቅስቃሴ» በሚል ስም እየተንቀሳቀሰ ያለው ኑፋቄ[7] በዋነኛነት ሊጠቀስ ይችላል:: ብዙ ወጣቶች ትምህርታቸውን ሳይመረምሩ በአምልኮ ዘይቤአቸው ተታለው ተወስደዋል፣ ይበልጡን የሚያሳዝነው የትምህርቱን ስንኩፍ ከሰለባዎቹ ልብ ነቅሎ ለማውጣት እጅግ አዳጋች መሆኑ ነው::

መናፍቃን የእነርሱን ሥርዐተ አምልኮ መከተልና ፕሮግራማቸውን በተከታታይ መካፈል፣ ለመንፈሳዊ እርካታ እምብርት እንደሆነ ይናገራሉ::

## 6. ለአእምሮ ጥያቄዎች መልስ መስጠት

ሰዎች በተለይም ወጣቶች መናፍቃንን የሚከተሉት ለጥያቄዎቻቸው መልስ ለማግኘት ብለው ነው፤ በዚህ ረገድ የይሖዋ ምስክሮችን መጥቀስ እንችላለን:: የይሖዋ ምስክሮች የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣናዊነት ያለምንም ገደብና ቅድመ ሁኔታ እንደሚያምኑ ይናገራሉ:: ሆኖም የግሪክና (ጽር) የዕብራይስጥ ጽሑፎችን እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ለአስተምህሮአቸው በሚመች መልኩ አጣመው ያቀርባሉ[8]:: የአቀራረባቸውም ስልት ማራኪና በኀብረ ቀለማት ያሸበረቀ ስለሆነ፣ ዕውቀት ፈላጊው ሰው በዚህ ሁኔታ በቀላሉ ይታለላል::

## 7. ሁለገብ የሆነ አኗኗር

አንዳንድ ሰዎች መናፍቃንን የሚከተሉት በአኗኗራቸው ፈጣን ለውጥ ወይም መሻሻል ስለሚያሳዩ ነው:: የሲጃራ፣ የመጠጥና የአደንዛዥ ዕፅ ሱስ ያለበት ሰው በመናፍቃን ግብረ ገብ ሊሳብ ይችላል:: ምክንያቱም መናፍቃን ቅድስናን አድርግና አታድርግ በሚል

[6] እያንዳንዱ የይሖዋ ምስክር ይህን ሥራ ስለሚሠራ፣ «አስፋፊ» የሚል ስም ተሰጥቶታል::

[7] ይህ መናፍቃዊ ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሾልኮ በመግባት አገልጋዮችን ጨምሮ ብዙ ምዕመናን በትምህርቱ እየተበከሉ ይገኛሉ:: ትምህርቱ እያስከተለ ያለውም ችግር በቀላል የሚገመት አይደለም::

[8] ተስፋዬ ሮበሌ በሥላሴ ማመን አይገባህምን? በሚል ርእስ የጻፈውን መጽሐፍ ይመለከቷል::

ቅድመ ሁኔታ ስለሚገድቡት ነው:: በእኩይ ግብረ ገብ የተቸገረ ሰው በእንዲህ ዐይነቱ የሥራ ቅድስና ትምህርት በቀላሉ ሊሳብ ይችላል::



# ክፍል ስድስት
# የመናፍቃንን ዕድገት ለመቀነስ ልንወስዳቸው የሚገቡ ርምጃዎች የትኞቹ ናቸው?

## ሀ. ሰዎች መናፍቃንን እንዳይከተሉ እንዴት ልንጠብቃቸው እንችላለን?[1]

ሰዎች መናፍቃዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ገብተው ከመንፈቃቸው በፊት፣ ወደዚያ የሚወስዳቸውን መንገድ ማጠር ጠቀሜታው እጅግ ታላቅ ነው:: ሰዎች በመናፍቃን ተታለው ከመወሰዳቸው በፊት ልንወስዳቸው የሚገቡ መሠረታዊ እርምጃዎች አሉ:: በመሠረቱ ከዚህ በታች የምንመለከታቸውን ዘዴዎች መጠቀም አስፈላጊ ቢሆንም፣ እነዚህን ዘዴዎች ብንጠቀም እንኳ ሰዎች መናፍቃንን ሊከተሉ ይችላሉ:: ሰዎች መናፍቃንን እንዲከተሉ የሚያስገድዳቸውን ሁኔታዎች ማጥበብ ይቻላል፤ ነገር ግን ፈጽመን መዝጋት ወይም ማጠር አንችልም::

---

[1] ይህ ክፍል የተወሰደው ተስፋዬ ሮበሌ የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን (ራእይ አሳታሚ ድርጅት፡ አዲስ አበባ 1991) ገጽ 155-158 ከሚባለው መጽሐፍ ሲሆን፣ ጸሓፊው አብዛኛውን መረጃ ያገኘው Alan W. Gomes, Unmasking the Cults ( Grand Rapids: Zondervan, 1995) ገጽ 86-90 ከሚባለው መጽሐፍ ነው::

## ለ. መናፍቃን ሐሰተኞች መሆናቸውን ለቤተ ክርስቲያንህ ማሳየት

### 1. ቤተ ክርስቲያን ከመናፍቃን ልትማር ይገባታል

መናፍቃን ሐሰተኞች ስለሆኑ፣ «ከእነርሱ የምንማረው አንዳች ነገር የለም» ብሎ ማሰብ ተላላነት ነው:: መናፍቃን ሰዎችን መሳብ የቻሉት (እየሳቡም ያሉት ) እውነት ባይሆንም እንኳ፣ ሰዎች የሚፈልጉት ነገር በእነርሱ ዘንድ ስላለ ነው::

መናፍቃን ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጡት በቤተ ክርስቲያን ደካማ ጐኖች ላይ ስለሆነ፣ ለእነርሱ ዕድገት ምክንያት የሆኑትን ነገሮች በመመርመር ቤተ ክርስቲያን ድካሟን አሻሽላ መቅረብ አለባት:: ብዙ ሰዎች መናፍቃንን የሚከተሉት በሕይወታቸው ለሚገጥማቸው ተገቢ ጥያቄ መልስ ለማግኘት እስከ ሆነ ድረስ፣ ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ፍላጎቶች በማጥናት፣ ቃለ እግዚአብሔር እነዚህን ፍላጎቶች በሚመልስበት ( በሚያረካበት) መልኩ ልትመልስ ይገባታል:: ቤተ ክርስቲያን፣ «ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ መናፍቃን ዘንድ ለጥያቄዎቻቸው መልስ ያገኙት ለምንድን ነው?» ብላ ራሷን መጠየቅ ይገባታል:: ቤተ ክርስቲያን፣ መናፍቃን ለሰዎች ጥያቄ የሚሰጡትን መልስ ልትሰማ፣ እነዚህን ጥያቄዎች ጌታ በመለሰበት መንገድ ልትመልስ ይገባታል::

ሰዎች መናፍቃንን የሚከተሉት ተገቢ የሆነውን አእምሮአዊ፣ ማኅበራዊ፣ ስሜታዊና መንፈሳዊ ፍላጎታቸውን ለማርካት ከሆነ፣ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ፍላጎቶች በሚያ ረካበት መንገድ በማርካት፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ክርስትና በቤተ ክርስ ቲያን ማጉልበት አለብን::



### 2. የአባሎቻችንን አእምሮአዊ ፍላጎት ማርካት አለብን

ክርስቲያን የሚያምነውን እንዲሁም ለምን በዚህ መልኩ ማመን እንደሚገባው ጠንቅቆ ማወቅ አለበት:: ዋልተር ማርቲን እንደሚለው ብዙ ሰዎች የሚያምኑትን ይወቁ እንጂ፣ ለምን በዚህ መልኩ ማመን እንደተገባቸው በጭራሽ አያውቁም:: እንዲያውም የበለጠ ቍጥር ያላቸው ምን እንደሚያምኑም ሆነ ለምን በዚህ መልኩ ማመን እንዳስ ፈለጋቸው ጨርሶ አያውቁም::

ክርስቲያን በእምነት እውነት ላይ ሊተከል፣ ጸንቶም ሊቆም ይገባዋል:: ማንኛውም ክርስቲያን አስተምህሮተ ሥላሴን፣ የክርስቶስን ፍጹም ሰብአዊነትና አምላካዊነት፣ ክርስቶስ በአካለ ሥጋ ከሙታን መነሣቱን እንዲሁም ደኅንነት በእምነት አማካይነት በጸጋ ብቻ የሚሰጥ መሆኑን ከቃለ እግዚአብሔር የተደገፈ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል::

ክርስቲያን ምን እንደሚያምንና ለምን በዚህ መልኩ እንደሚ ያምን ከመጽሐፍ ቅዱስ መከላከያ ነጥብ ማቅረብ ካልቻለ፣ ለመናፍቃን እንቅስቃሴ የተጋለጠ ነው:: ማርቲን እንደሚለው፣« ከመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር ለዘጠና ቀን የቆየ የይሖዋ ምስክር መካከለኛ ዕውቀት ያለውን (avarage) ክርስቲያን በዐሥራ አምስት ደቂቃ ውስጥ እምነቱን ሊያስጥለው (በእጅ ሊያስገባው) አሊያም ከፉኛ ሊያደናግረው ይችላል»:: እውነት ጠልቆ የገባው አማኝ በማስረጃ ተብዬዎቹ አይሞኝም:: የባንክ ሠራተኞች ከጤናማው ብር ጋር የዕለት ተዕለት ቅርርብ ስላላቸው፣ ከጤናማ ብሮች መካከል ሐሰተኛ ኖቶችን (ብሮችን) ነቅሰው ያወጡአቸዋል:: እንደዚሁም ክርስቲያኖች የመናፍ ቃንን ስሕተት ለማወቅም ሆነ፣ ለጥያቄአቸው በቂ መልስ ለመስጠት እውነተኛውን አስተምህሮ እንደሚገባው ማወቅ ይኖርባቸዋል::

ክርስቲያን ከፀሓይ በታች ያሉትን የመናፍቃን አስተምህሮ ሁሉ ማወቅ አያስፈልገውም። ነገር ግን ዋና ዋና መናፍቃንንና የመናፍቃንን ተመሳሳይ ባሕርያት ማወቅ ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው።

ቤተ ክርስቲያን በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ትኩረት ስትሰጥና በመናፍቃን ለተጐዱት ሰዎች የማገገሚያ ትምህርት ስታስተምር [አሁን ይህም እየተረሳ እንደመጣ ይታያል]፣ ጊዜዋንና ጉልበቷን በከንቱ ስታባክን፣ ኑፋቄ የብዙዎችን እምነት ሰብሮ መግባቱ ብዙ ላያስደንቅ ይችላል።

ሰዎች እምነታችንን በተመለከተ የሚጠይቁንን አእምሮአዊ ጥያቄ በበቂ ሁኔታ መመለስ ካልቻልን፣ ከባድ አጣብቂኝ ውስጥ እንደምንገባ ማወቅ አለብን ነው የሚገጥመን። ዋቢ ይሆነን ዘንድ አንድ ምሳሌ እንጠቀም፤ አንዲት እኅት ለአንድ ሙስሊም ስለ ክርስቶስ አዳኝነት ልትነግረው ፈለገች እንበል፤ ሙስሊሙ፣ አምላኳ እንዴት አንድም ሦስትም እንደሆነ እንድታብራራለት ፈለገ። እርሷም፣ «ሥላሴ ልታምነው የሚገባህ ጉዳይ ነው። ነገር ግን ይህ ትምህርት እንዲገባህ በጾም በጸሎት፣ በእግዚአብሔር ፊት ስትወድቅ እግዚአብሔር ራሱ ይገልጽልሃል» አለችው።

ከዚህ ውይይት ብዙ ነገር መመልከት ይቻላል። አንደኛው ልጆቹ የሥላሴ ትምህርት ስሜት የማይሰጥ፣ የትምህርተ መለኮትም ሆነ የአመክንዮ መሠረት የሌለው፣ ነገር ግን ጭፍን በሆነ እምነት የሚታመን ነው ያደረገችው። ሌላው፣ «በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ» (1ጴጥ 3÷15) የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ አልኖረችበትም።



ቤተ ክርስቲያን ስለ መናፍቃንና ስለ አስተምህሮአቸው ተግታ ማስተማር ያስፈልጋታል። ቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች ቅድሚያ በመስጠት፣ የመናፍቃንን መሠረተ እምነት እንዲሁም የተለያዩ ሃይማኖታዊ ድርጅቶች ምን እንደሚያምኑና ለምን በዚያ መልኩ እንደሚያምኑ ማስተማር ይገባታል። ይህም ትምህርት ክርስቲያኖች ለምስክርነት ብቁና ዝግጁ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ተቃውሞአቸውንም ለመመለስ የምናጠናው ጥናት፣ እምነታችንንም ሆነ ዕውቀታችንን ያጠነክረዋል።

ቤተ ክርስቲያን፣ ሰዎች በጥልቀት እንዲያስቡ የሚረዳቸውን እንደ ሥነ አመክንዩ (Logic) ያሉ ትምህርቶችን ልታስተምር ይገባል። ምናልባት ምን ማመን እንዳለባቸውና የትኛውን ማመን እንደሌለባቸው ማስተማር ብቻ በቂ ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እውነቱን ከሐሰቱ የሚለዩበትን ዘዴ ማሳወቅ እጅግ ጠቃሚ ነው።

ክርስቲያን እውነትን የሚገመግምበትን፣ ሐሰትን በቀላሉ ነቅሶ የሚያወጣበትን ዕውቀት ካለገኘ፣ « በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ» የሚለውን ትእዛዝ ተግባራዊ ማድረግ ይቸግረዋል።

« እንደ ስሕተት ሽንገላ ባለ ተንኰል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህ እየተንሳፈፍን ሕፃናት መሆን ወደፊት አይገባንም» ( ኤፌ 4÷14)።

## *3. የአባሎቻችንን ማኅበራዊና ስሜታዊ ፍላጎቶች ማርካት አለብን*

የቤተ ክርስቲያንን አባሎች መንፈሳዊ ጥማት ለማርካት የቤተ ክርስቲያንን መሠረተ እምነቶች አጠናክረን ልናስተምር ይገባል

(1ጴጥ 2÷2፤ 2ጢሞ 3÷16) :: በተጨማሪም አእምሮንና ስሜትን ሊነካ የሚችል አምልኮ መፍጠር አለብን::

መናፍቃን ቅናት [Zeal] አላቸው:: ነገር ግን ቅናታቸው ያለ እውነተኛ ዕውቀት ነው (ሮሜ10÷2):: በተቃራኒው እውነተኛ ክርስቲያኖች እውነትን ይዘው ሳለ ጻተኛነት ይስተዋልባቸዋል:: በሚዛናዊነት የተሞላው የቃለ እግዚአብሔር ትምህርት ግን ቅናት ከዕውቀት ጋር ያቀናጀ ነው ( 2ጴጥ 1÷ 3-8)::



## ሐ. መናፍቃን ሐሰተኞች መሆናቸውን ለልጆችህ ማሳየት

### 1. ጠንካራ ቤተ ሰብ ልጆቹን ከመናፍቃን በመጠበቅ ቊልፍ ሚና ይጫወታል

ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር በማንኛውም ጒዳይ ላይ በግልጽ መወያየትን ባህል ካደረጉ፣ መንፈሳዊውን ነገር ለመወያየት አዳጋች አይሆንባቸውም:: በርግጥ ልጆች ስለተለያዩ መናፍቃንም ሆነ ሃይማኖቶች የመስማት ፍላጎት ላይኖራቸው ይችላል፤ ነገር ግን መልካም ግንኙነት ለውይይት ጥሩ መሠረት ነው::

ስለ እምነትህ ከልጆችህ ጋር በግልጽ ተወያይ:: ወላጆች ልጆቻቸውን በተመለከተ ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ የማስተማርም ሆነ መመሪያ የመስጠት ተቀዳሚ ኀላፊነት አለባቸው (ኤፌ 6÷4):: ስለዚህ ተቀደሚ ኀላፊነታቸውን በሰንበት ትምህርት አስተማሪዎች ትከሻ ላይ ብቻ መጣል አግባብ አይደለም:: ልጆችን በእግዚአብሔር መንገድ እየመሩ ማሳደግ ቀዳሚው የወላጆች ኀላፊነት መሆኑን መገንዘብ ያሻል::

### 2. እንደማንኛውም ግለሰብ ልጆችህን አክብር

ልጆች እንደማንኛውም ግለሰብ እንዲከበሩ ይፈልጋሉ:: ከወላጆቻቸውም የተለየ ማንነት አላቸው:: ወላጆች ልጆቻቸው ማንነታቸውን ሊገልጹ የሚፈልጉበትን ተገቢውን ነጻነት ሊነፍጓቸው አይገባም:: ልጆች ይህን የሚያጡ ከሆነ፣ ወደ መናፍቃን እንዲሄዱ ሊገፋፋቸው ይችላል:: መናፍቃንን በመከተል ከቤተሰቦቻቸው የተለየ ማንነት እንዳላቸውና የተለየ የአኗኗር ዘይቤ እንደሚከተሉ ማሳያ መንገድ

በእያንዳንዱ አስተምህሮ ሐሰቱንና እውነቱን ጠልቀን ባናስተምራቸውም፣ በሚገጥሟቸው አጋጣሚዎች ሁሉ የሚረዱአቸውን ዘዴዎች ማስተማር በቂ ነው:: ዘዴዎች ማንኛውንም ነገር የምንመዝንባቸው መሣሪያዎች ናቸውና::

# ክፍል ሰባት
# የይሖዋ ምስክሮች ከየት እስከ የት?

## ሀ. የይሖዋ ምስክሮች ታሪካዊ ዳራ[20]

የይሖዋ ምስክሮች ታሪክ ከመሥራቹና ከመሪዎቹ ታሪክ ጋር የተቈራኘ ስለሆነ፣ የእነዚህን ግለሰቦች ታሪክ ማወቅ የድርጅቱን ታሪክና አስተምህሮ ለማወቅ ጥሩ መደላደል ይሆናል::

### «መጋቢ» ቻርልስ ታዝ ራስል (1882-1961)

መጋቢ ቻርልስ ታዝ ራስል በቀድሞዋ አልገኒ፣ አሁን የፒትስበርግ አካል በሆነችው በፔንሲልቫኒያ የካቲት 16 ቀን 1852 ዓ.ም ተወለደ:: ራስል በ15 ዓመቱ ከአባቱ ጋር በአክስዮን የልብስ መሸጫ መደብር ከፈተ:: በዚህን ወቅት ነው ቤተሰቦቹ አባል የሆኑበትን የፕርስቢቴሪያንን ቤተ ክርስቲያን በመተው፣ የማኅበረ ምእመናን ቤተ ክርስቲያን አባል የሆነው::

ይሁን እንጂ ራስል በዚህ ቤተ ክርስቲያን ይሰጡ ከነበሩት አስተምህሮዎች፣ በተለይ በዘላለም ቅጣትና (ኵነኔና) በቅድመ ምዳቤ ትምህርቶች እጅግ ተቸገረ:: በዚህም ምክንያት በ17 ዓመቱ ወደ ክህደትና መጽሐፍ ቅዱስን ወዳለመቀበል ደረጃ ደረሰ::

---

[20] ይህ ክፍል የተወሰደው ተስፋዬ ሮበሌ፣ የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃል እግዚአብሔር ሲመዘን ከሚለው መጽሐፍ ሲሆን፣ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ይህን መጽሐፍ ይመለከቷል::

ከዚያም ራስል በፒትስበርግ ስድስት ሰዎች የሚገኙበትንና በየጊዜው ለመገናኘት የወሰነውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን በ1870 ዓ.ም አደራጅቶ መራ:: በዚህን ወቅት ራስልና ጓደኞቹ ክርስቶስ በሥጋ ዳግም ይመጣል የሚለው ትምህርት ስላልተዋጠላቸው፣ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ረቂቅና (መንፈሳዊና) በዐይን ሥጋ የማይታይ መሆኑን ለማሳመን ራስል ፣ « ዘ አብጀክት ኤንድ ማነር ኦፍ ዘ ሎሪድስ ሪተርን» በሚል ርእስ 50ሺህ ቅጅ በራሪ ጽሑፎችን አዘጋጀ::

በ1876ዓ.ም ራስል ከሮቸስተሩ ኤን ኤች ባርቦር ጋር ተገናኘ፤ ባርቦር ከአድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን አፈንግጠው ለወጡ ሰዎች መሪ ነበር:: ያፈነገጡበትም ምክንያት ራስል የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ረቂቅ (መንፈሳዊ) /የማይታይ/ ነው፣ በሚለው ትምህርቱ በማመናቸው ነበር:: ከዚያም ራስል ይመራው የነበረው የፔትስበርግ ኅብረትና ባርቦር ይመራው የነበረው የሮቸስተር ኅብረት ተቀላቀለ:: ይህም፣ «ዘ ሄራልድ ኦፍ ዘ ሞርኒንግ» ለተባለው መጽሔት መውጣት ምክንያት ሆነ::

ከጥቂት ዓመታት በኋላ፣ ራስል ከባርቦር ጋር የነበረውን ግንኙነት አቋረጠ:: ምክንያቱም ራስል የክርስቶስ የማዳን ሥራ አዳምንና የእርሱን ዝርያዎች ይጨምራል ብሎ ስለሚያምን ነበር::

በ1881 ዓ.ም «የመጠበቂያ ግንብ የትራክት ማኅበር» በራስል አስተዳዳሪነት ተመሠረተ:: ይህ ስም በ1896ዓ.ም «የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር» በሚለው ስያሜ ተለወጠ:: እንግዲህ ይህን ቀን ነው የድርጅቱ ሕጋዊ ጅማሬ የምንለው::

ራስል 7 ቅጽ ያላቸው ተከታታይ የአስተምህሮ መጻሕፍትን ጽፎአል:: የመጀመሪያው ቅጽ ለንባብ ያበቃው በ1886 ዓ.ም ሲሆን፣ የመጽሐፉም ርእስ፣ «ዘ ዲቫይን ፕላን ኦፍ ዘ ኤጅ» የሚል ነበር:: ሰባቱም ቅጽ መጻሕፍት በመጀመሪያ የተሰየሙት፣ «ሚሊኒያል ዳዎን» በሚል ስየሜ ሲሆን፣ በኋላም፣ «ስተዲስ ኢን ዘ ስክሪፕቸርስ» ተባሉ:: እነዚህ መጻሕፍት ከፍተኛ ሥርጭት የነበራቸው ሲሆን፣ የመጀመሪያው ቅጽ ከ 6 ሚሊዮን ቅጅ በላይ ታትሞ ተሠራጭቶአል::



ራስል በ1979 ዓ.ም ሚሪያ ፍራንሴስ አክሊ የተባለች ሴት አገባ:: ራስል በዚህ ጋብቻ ልጅ አልወለደም:: ሚስስ ራስል ለብዙ ዓመት የመጠበቂያ ማኅበር ገንዘብ ያዥና ጸሓፊ፣ የ «መጠበቂያ ግንብ» መጽሔት ረዳት አዘጋጅ ሆነው ሠርተዋል:: በ1897 ዓ.ም ራስልና ሚሪያ ተፋቱ::

በ1913 ዓ.ም ሚስስ ሚሪያ፣ «ባላቸው ያደርስባቸው ስለነበረው ጭቆናና ከሌሎች ሴቶች ጋር ስለ ነበረው አላስፈላጊ ግንኙነት» በመጥቀስ ራስልን በፍርድ ቤት አቁመውት ነበር::

ራስል ጥቅምት 31 ቀን 1916 ዓ.ም በቴክሳስ ክፍለ አገር ሞተ::

## «ዳኛው» ጆሴፍ ፍራንክሊን ሮዘርፎርድ
## *(1869 - 1942)*

ቻርልስ ታዝ ራስል ሲሞት፣ በእርሱ የአስተዳደር ዘመን የድርጅቱ የሕግ አማካሪ የነበረው፣ ጆሴፍ ፍራንክሊን ሮዘርፎርድ የድርጅቱ ሁለተኛ ፕሬዝዳንት ሆነ:: ሮዘርፎርድ ኅዳር 6 ቀን 1869 ዓ.ም የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን አባል ከነበሩት ቤተሰቦቹ በቦንቬል ሚዞሪ ተወለደ:: በተወለደ በ16 ዓመቱ የሕግ ትምህርት ለመማር ኮሌጅ ገባ:: በ22 ዓመቱ የፍርድ ቤት በዳኝነት መሥራት ጀመረ:: ለዚህም ነው ሮዘርፎርድ፣ «ዳኛው» የተባለው::

ሮዘርፎርድ ከመጠበቂያ ግንብ ባለሥልጣናት ጋር ግንኙነት የጀመረው በ1894ዓ.ም ነበር:: ወደ እንቅስቃሴው የገባው በ1906 ዓ.ም ሲሆን፣ የድርጅቱ የሕግ አማካሪ የሆነው ደግሞ በ1907ዓ.ም ነው::

ሮዘርፎርድ የፕሬዝዳንትነቱን መንበር እንደያዘ የብሩክሊኑን ቢሮ የአስተዳደር መዋቅር በመቀየር የድርጅቱ አባላት ወደ መስክ አገልግሎት እንዲያተኩሩ አደረገ::

ራስል በሞተ ማግስት በድርጅቱ ባለሥልጣናት መካከል የሥልጣን ሽኩቻ ተፈጠረ፣ የችግሩ ምክንያት ናቸው የተባሉትም ሰዎች ከሥልጣናቸው ተባረሩ።

የሮዘርፎርድ የመጀመሪያው መጽሐፍ «ዘ ሃርፕ አፍ ጎድ» [«የእግዚአብሔር በገና»] በ1921ዓ.ም ታትሞ ወጣ። ሮዘርፎርድ ከራስልም ይልቅ ብዙ መጻሕፍትን ያጻፈ ሰው ነበር። እነዚህም መጻሕፍት የራስልን መጻሕፍት የሚተኩ፣ በድርጅቱ አስተምህሮ ላይ የተመሠረቱ መጻሕፍት ነበሩ።

1920 ዓ.ም የድርጅቱ አባላት በሙሉ የመስክ ምስክርነታቸውን በተመለከተ ሳምንታዊ ሪፓርት እንዲያደርጉ ተወሰነ። በራስል የአስተዳደር ዘመን ድርጅቱ ትኩረት የሚሰጠው በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች፣ በባሕርይ ዕድገትና በመንፈስ ፍሬዎች ላይ ነበር። አሁን ይህ ሁሉ ቀርቶ የድርጅቱን ጽሑፎች በማሠራጨትና ስለ የቀኑ ሥርጭት ውሎ ለዋናው መሥሪያ ቤት ሪፓርት ወደ ማድረጉ ተለወጠ። በዚህም ምክንያት ሦስት አራተኛ የሚሆኑት፣ «የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች» ድርጅቱን ለቀው ወጡ።

በ1931 ዓ.ም በኮሎምቦስ ኦሀዮ በተደረገው ስብሰባ የድርጅቱ አባላት፣ «የይሖዋ ምስክሮች» ተባሉ። ይህ ስያሜ የተወሰደው ከኢሳ 43÷10 ላይ ነው፣ «እናንተ የመረጥሁት ባሪያዬ ምስክሮቼ ናችሁ ይላል እግዚአብሔር»።

ከ1940 ዓ.ም ጀምሮ፣ «መጠበቂያ ግንብ» እና «ንቁ» የሚባሉት መጽሔቶች በየመንገድ ዳር በአባላቱ መሠራጨት ጀመሩ። ይህ የማሠራጨት ፖሊሲ እስካሁን እንዳለ ነው (ለዚህም ነው የይሖዋ ምስክሮችን በየቤቶቻችን በሮች ላይ እና በየመንገድ ዳሩ ሲንከላወሱ የምናያቸው)።

ሮዘርፎርድ ድርጅቱን ለ25 ዓመት ከመራ በኋላ ጥር 8 ቀን 1942 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።



## *ናታን ሆመር ኖር (1905 - 1977)*

ጆርጅ ፍራንክሊን ሮዘርፎርድ ሲሞት፣ ናታን ሆመር ኖር ጥር 13 ቀን 1942 ዓ.ም የድርጅቱ ሦስተኛ ፕሬዝዳንት ሆኖ ተመረጠ።

ኖር በ1905ዓ.ም በቤተ ልሔም ፔንሲልቫኒያ ተወለደ። በ16 ዓመቱ የተሐድሶ ቤተ ክርስቲያን አባልነቱን በመተው፣ አሊንቶን ፔንሲልቫኒያ ከሚገኘው የይሖዋ ምስክሮች ጉባኤ ጋር ተቀላቀለ። በ18ዓመቱ የድርጅቱ የሙሉ ጊዜ ሰባኪ እንዲሁም ብሮክሊን በሚገኘው ዋና መሥሪያ ቤት አባል ሆነ። በ1932ዓ.ም የድርጅቱን የኅትመት እንቅስቃሴዎች ሁሉ እንዲያስተባብር የኅትመት ቢሮው አስተዳዳሪ ሆነ። በ1934 ዓ.ም የኒውዮርክ ኮርፖሬሽን ምክትል ዳሬክተር ሆነ።

ኖር ከእርሱ በፊት እንደ ነበሩት የድርጅቱ ፕሬዝዳንቶች፣ ዕውቅ ሰው አልነበረም። ከአሜሪካን ውጪ ያሉ አንዳንድ የድርጅቱ አባላት፣ ስሙን እንኳ አያውቁም ነበር። በሥልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ ዐላማው አድርጎ የተንቀሳቀሰው የትምህርት ፕሮግራሞችን ማሳደግ ነበር። የ «ጊልአድ (የገለዓድ) የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዳስ ትምህርት ቤት» በ1943ዓ.ም የተቈረቈረው በእርሱ የፕሬዝዳንትነት ዘመን ነበር።

በኖር የፕሬዝዳንትነት ዘመን በርካታ የአስተምህሮ መጻሕፍት ተጽፈዋል። ከዚህ በፊት እንደ ነበሩት የድርጅቱ መጻሕፍት ሁሉ፣ እነዚህም መጻሕፍት በአንድ ግለሰብ የተጻፋ አልነበሩም። መጻሕፍቱ በሚስተር ኖር ተጽፈው ከኅትመት በፊት የተለያዩ ሰዎች አይተዋቸዋል። እነዚህ መጻሕፍት የራስልንና የሮዘርፎርድን መጻሕፍት የተኩ ነበሩ። ከእነዚህም መጻሕፍት መካከል በ1943 ዓ.ም የታተመው፣ «እውነት ዐርነት ያወጣሃል» እንዲሁም በ50 ቋንቋዎች 17ሚሊዮን ቅጅ ተባዝቶ የተሠራጨው፣ «እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን» የሚሉት መጻሕፍት ይገኙበታል።

በኖር የፕሬዝዳንትነት ዘመን ከተሠሩት ሥራዎች መካከል ወደ እንግሊዝኛ ተተረጐመ የሚባለው መጽሐፍ ቅዱስ ነው:: ይህ መጽሐፍ በመጀመሪያ የታተመው በ1950ዓ.ም ሲሆን፣ «ዘ ኒው ወርልድ ትራንስሌሽን ኦፍ ዘ ክርስቲያን ግሪክ ስክሪፕቸር» («የአዲሱቱ ዓለም ትርጒም») በመባል ይጠራል:: ይህ መጽሐፍ ሥርጭቱ አልተጀመረም እንጂ በ1993 ዓ.ም ወደ አማርኛ ተተርጒሞአል::

ይህን መጽሐፍ ወደ እንግሊዝኛ የተረጐሙት እነማን እንደሆኑ፣ የግሪክና የዕብራይስጥ ዕውቀታቸው እስከ ምን ድረስ እንደሆነ፣ እስከ ዛሬ ከድርጅቱ የተሰጠ ማብራሪያ የለም:: ነገር ግን እጅግ በርካታ የዕብራይስጥና የግሪክ ቋንቋ ሊቃውንት ትርጒሙን «ለድርጅቱ አስተምህሮ ሎሌነት ያደረ ነው» በሚል፣ በአንድ ድምፅ ኰንነውታል:: በርግጥም መጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን፣ ከድርጅቱ አስተምህሮ ጋር እንዲጣጣም ተደርጐ የተዘጋጀ የድርጅቱ የእምነት አቋም መግለጫ ነው:: ናታን ሆመር ኖር በ1977 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞተ ተለየ::

## *ፍሬድሪክ ዊሊያም ፍራንዝ*
## *(1893 - 1992)*

ናታን ሆመረ ኖር በ1977ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ፣ ሲሞት፣ በእርሱ የፕሬዝዳንትነት ዘመን እንደ ትልቅ የትምህርተ መለኮት ምሁር ይቈጠር የነበረው ፍሪድሪክ ዊሊያም ፍራንዝ፣ የድርጅቱ አራተኛ ፕሬዝዳንት ሆነ:: በዚህ ሰው የአስተዳር ዘመን ነበር፣ የይሖዋ ምስክሮች ለትምህርታቸው ማስረጃ የሚሉአቸውን ጥቅሶች መጥቀስ የጀመሩት::

ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ ድረጅቱ በታላቅ ቀውስ ውስጥ ስለ ወደቀ፣ ብዙ የአስተዳደር አባላት የፍራንዝን የወንድም ልጅ፣ ሬምንድ ፍራንዝን ጨምሮ፣ ለድርጅቱ ታማኝ አይደላችሁም በሚል ከሥራ



ተባረሩ:: ነውጡን ያስከተሉት ብዙ ምክንያቶች ቢሆኑም ዋነኛው ግን በድርጅቱ አስተምህሮ ላይ የነበረው አለመግባባት ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል:: ከእነዚህም አስተምህሮዎች ውስጥ ድርጅቱ ነገረ ምጽአትን በተመለከተ ያወጣቸው አኃዛዊ ትንቢቶች፣ ዳግም ልደት ለ144ሺዎቹ («ለቅቡዓን») ብቻ እንጂ ለበጎች አያስፈልግም፣ የሚለው ትምህርት ይገኝበታል::

ፍራንዝ በ1992 ዓ.ም ሲሞት፣ አሁን የእርሱን የፕሬዝዳንትነት ቦታ ተክቶ ያለው በፍራንዝ አስተዳደር ዘመን የአመራር አካል የነበረው ሚልተን ጂ ሔንሼ ነው::

## *ለ. የይሖዋ ምስክሮች ታሪክ በኢትዮጵያ*[21]

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የይሖዋ ምስክር ኪሪኮር አታዛኮርታዚያን (Krikor Hatzakortazian) የተባለ አርመናዊ ነው:: አታዛኮርታዚያን በ1935ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ የገባው የመጀመሪያው የይሖዋ ምስክር ይሁን እንጂ፣ ብሮክሊን ከሚገኘው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የተላከ የድርጅቱ ሚስዮናዊ አልነበረም::

በመጠበቂያ ግንብ ዋና መሥሪያ ቤት ተልከው ወደ ኢትዮጵያ የመጡት የመጀመሪያዎቹ ሚስዮናውያን ኢትዮጵያ የደረሱት በ1950ዓ.ም ነበር:: እነዚህ ሚስዮናውያን ጊልአድ [ገለዓድ] በመባል በሚታወቀው የድርጅቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብተው የተማሩ ነበሩ::

---

[21] ሰሎ ዘገባ ከፈለጉ ተስፋዬ ሮበሌ የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በሚል ርእስ የጻፈውን መጽሐፍ ይመለከቷል::

በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የነበሩት፣ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ በአገሪቱ ውስጥ ያሉት ሚስዮናውያን ሁሉ በመላው ኢትዮጵያ እንዲያስተምሩ ፈቃድ ሰጡ። ይህ ጥሪ ይሖዋ ምስክሮችንም ያካተተ ነበር። የይሖዋ ምስክሮች አዲስ አበባ በሚገኘው የንግድ ሥራ ኮሌጅ ለማስተማር መፈለጋቸው ወደ አገሪቱ የመግባት ምክንያት ሆነ። ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ከነበረው፣ «መደበኛ ፖሊሲ የተለየ» ነበር። ሁሉም ሚስዮናውያን እምነቱን ለማስፋፋት የሚጠቀሙበት ዘዴ በሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ ስብከት ማካሄድ ሳይሆን፣ ከትምህርት ክፍለ ጊዜ በኋላ፣ ፈቃደኛ የሆኑትን ተማሪዎች ወደ ቤታቸው በመጋበዝ ስለ እምነታቸው ማስተማር ነበር።

በ1953 ዓ.ም ሚስዮናውያኑ ይከተሉት የነበረውን እምነቱን የማስፋፋት ዘዴ በመቀየር፣ በየመንገዱ ላይ የተገኘውን ወጭ ወራጅንና ዐላፊ አግዳሚውን ብቻ ሳይሆን፣ የሰዎችንም ቤት ማንኳኳት ጀመሩ። የይሖዋ ምስክር ለመሆን ካልወሰኑ ሰዎች ጋርም የሚደረገው ጥናት እንዳይራዘም ወሰኑ።

የሰዎችን ቤት በማንኳኳት በተካሄደው የመስክ አገልግሎት የተገኙት የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት በ1953 ዓ.ም ተጠመቁ። በዚህ ጊዜ ነበር የወቅቱ የይሖዋ ምስክሮች ፕሬዝዳንት፣ ናታን ሆመር ኖር ለጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ የመጡት።

በ1950ዎቹ መካከል የመጠበቂያ ግንብ ሚስዮናውያን ከአዲስ አበባ ውጪም ሆነ ትምህርት ቤት ባቋቋሙባቸው ከተሞች እንዳይሰብኩ ተከለከሉ። በዚህ ጊዜ ብሮክሊን የሚገኘው ዋና መሥሪያ ቤት ኢትዮጵያውያኑን በአቅኚነት በማሠልጠን ከአዲስ አበባ ውጪ ባሉ ስፍራዎች በተኑ።



በ1950ዎቹ መካከል አዲስ መስፋፋት ከተደረገባቸው አካባቢዎች አንዱ ኤርትራ ነው [በወቅቱ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴራሲዮን ተቀላቅላ ነበር]። በ1956ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ የይሖዋ ምስክር ሚስዮናዊ ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ በመሄድ ሚስዮናዊ ሥራ ጀመረ፤ ጽሑፎችንም ለማሠራጨት ፈቃድ አገኘ።

የይሖዋ ምስክሮች በመጀመሪያ ስደት የደረሰብን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ነው ባዮች ናቸው። ቤተ ክርስቲያኒቱ በጉባኤ ኒቂያ በጽኑ የተኮነነውን አርዮስን እንደ ሰይጣን ቍራጭ (የሳጥናኤል ልጅ) ትመለከት ስለ ነበር፣ የአርዮስ መንፈሳዊ ልጆች የሆኑትን የይሖዋ ምስክሮችን አጥብቃ የመቃወሟ ምክንያት ይህ ሊሆን ይችላል።

በ1959ዓ.ም የኢትዮጵያ መንግሥት በኤርትራ የሚኙትን የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች እንዳይንቀሳቀሱ እንዲሁም በኢትዮጵያ የወጣው የዕገዳ ዐዋጅ በኤርትራም ተግባራዊ እንዲሆን አደረገ። በ1960ዓ.ም ሁሉም የይሖዋ ምስክር ሚስዮናውያን አገር ለቀው ወጡ።

ከ1960ዎቹ መካከል ጀምሮ የይሖዋ ምስክሮች አንጻራዊ ነጻነት ስላገኙ በየመንገዱ ላይም ሆነ የየሰውን በር በማንኳኳት እምነታቸውን መስበክ ጀመሩ። በ1961ዓ.ም «እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን»፣ በ1973ዓ.ም «ወደ ዘላለም ሕይወት የሚመራው እውነት» እንዲሁም፣ «የእውነተኛ ሰላምና ጥበቃ ምንጩ የቱ ጋ ነው?» [True Peace And Security-From What Source? »] የሚባሉ መጻሕፍት በአማርኛ ቋንቋ ታትመው ለንባብ ቀረቡ። በትግርኛ ቋንቋ ደግሞ፣ «የመንግሥት አደረጃጀት ስብከትና ደቀ መዛሙርት ማፍራት» [«Organization For Kingdom-Preaching And Disciple-Making »] የሚባለው መጽሐፍ ተዘጋጀ።

ያየነው የይሖዋ ምስክሮች በውጭ የተነሣባቸውን ችግር ቢሆንም እንኳ፣ ውስጣዊ አለመግባባቶችም ተፈጥረውባቸው ነበር:: በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት የነበረው የጴንጤቆስጤ ልምምድ ወደ አጥቢያ የይሖዋ ምስክሮች ጉባኤም ደርሶ ነበር:: ስለዚህም አንዳንድ የይሖዋ ምስክሮች ሰማያዊ ተስፋ ተቀብለናል ማለት ጀመሩ[22]::

ናይሮቢ ከሚገኘው ቢሮ ዊልያም ኒስበት (William Nisbet) የተባለው ሚስዮናዊ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ችግሩን ለመፍታት ቢሞክርም፣ አንዳንድ የይሖዋ ምስክሮች በአቋማቸው ስለጸኑ ከድርጅቱ ተባረዋል::

የይሖዋ ምስክሮች ያጋጠማቸው ሌላው ስደት፣ ከማርክሲስታዊው መንግሥት ነው:: ከ1980ዓ.ም እስከ 1980ዓ.ም በዓመታዊ መጽሐፋቸውም ሆነ፣ «መጠበቂያ ግንብ» በተባለው መጽሔታቸው ምንም ዐይነት ስታቲስቲካዊ ዘገባ ያለመቅረቡ የዚህ ውጤት ነው:: እንደ 1992ዓ.ም ዓመታዊ መጽሐፍ፣ ብዙ የይሖዋ ምስክሮች በእምነታቸው የተነሣ ተገድለዋል::

## ማጠቃለያ

ለይሖዋ ምስክሮች ዕድገት እንደ ምክንያት ከሚቈጠሩት መካከል፣ በስደት ጊዜ ጸንተው መቆማቸው፣ ሊስቡ የሚችሉና በወቅታዊ ርእሶች ላይ የሚዘጋጁ ጽሑፎቻቸው፣ እያንዳንዱ የይሖዋ ምስክር መሠረተ እምነቱን ማወቁ፣ አባላቱ እምነታቸውን ለሌላ ሰው ለማስተማር ያላቸው ከፍተኛ ፍላጎት እንደ ምክንያት ከሚቈጠሩት ውስጥ ዋንኞቹ ናቸው::

---

22 እንደ መጠበቂያ ግንብ አስተምህሮ ሰማያዊ ተስፋ የተቀበሉት፣«ቅቡዓን» ብቻ ናቸው::



# ክፍል ስምንት
# ትምህርተ ሥላሴ የተቀዳው ከቃለ እግዚአብሔር ወይስ ከአረማውያን መድበለ አማልክት?

## ሀ. የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮተ ሥላሴ

የይሖዋ ምስክሮች በትምህርተ ሥላሴ አያምኑም:: የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በመባል የሚታወቀው ድርጅታቸው፣ «ሰዎች ስለ ሥላሴ በቅድሚያ የሚያውቁት ነገር ሳይኖር፣ መጽሐፍ ቅዱስን ከዳር እስከ ዳር ቢያነቡት፣ ካነበቡት ነገር የሥላሴን ፅንሰ ሐሳብ ሊያገኙ ይችላሉን? በፍጹም አይችሉም»[1] ይላል:: እንዲሁም «ሌት ጎድ ቢ ትሩ» የሚባለው የድርጅቱ መጽሐፍ፣ «ይህ እንግዳ የሆነና የተወሳሰበ አደናጋሪ አስተምህሮ በክርስቶስ ኢየሱስ ምንምትኩረት አልተሰጠውም፣ አላብራራውም፣ አላስተማረውም» ይላል[2]:: እንዲሁም «ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር» የሚለው መጽሐፋቸው ደግሞ፣ «የሥላሴ ትምህርትም ሆነ ስለ አምላክ ያላቸው ፅንሰ ሐሳብ [የሥላሴ አማኞች] ከአረማውያን ምንጮች

---

[1] በሥላሴ ማመን ይገባሃልን? ( ብሮክሊን፣ የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክር ማኅበር፣ 1993) ገጽ 2

[2] " Let God Be True" ( Brooklyn : Watchtower Bible and Tract Society, 1952) ገጽ 200